*መታሰቢያነቱ፤ለርእሶም ገብረእግዚአብሔር***

# ውሃ ውሃ የሚሰያኝ ጉዞ

ብርሃነመስቀል ደጀኔ

**ይኽ የጉዞ ማስታወሻ (ኅዳር 1987 ዐ.ም) አስቀድሞውኑ የጉዞዬ ዋነኛ አንቂና ባለውለታዬ ጭምር ለኾነው ወዳጄ ልቤ ኢንጅነር ርእሶም ገብረእግዚአብሔር (1947-2005 ዐ.ም) መታሰቢያነት የቆመ ሲኾን፤በወቅቱም መጣጥፉ እርሱ በኃላፊነት ይሰራበት ለነበረው የውሃ ሥራዎች ዲዛይን ድርጅት (ተከዜ ፕሮጀክት) መጽሔት ላይ "ከበላይ-ከተከዜ ፕሮጀክት" በሚል ብርዕ ስም(*ርእሶምን?! ለማመላከት*) እንዲታተም አበርክቼው ሳይታተም የቀረ ጽሑፍ ነው። ተረኩን በዚኽ መንፈስ ኢንጅነር (ሃይድሮሎጂስት) እንዲተርከው ተወጥኖ የነበረ መኾኑንም ልብ ይሏል።

እግዞኦ! ውሃ ውሃ የሚሰኝ ጉዞ!!! ቀድሞ የኔን አጋጣሚ የተካፈለ ካለ ፥ ላይደነቅ ይችል ይኾናል። ይኹንና ያጋጠመኝ፥ ከመኪና ሆድ ሳይወጡ፥ ቀን ሙሉ ፈጅና ሳምንት በሌ፥ ተከታታይ ጉዞ ነበር። እንዲኽ ዓይነት ምድር ቆንጣጭና የተየለሌ ጉዞት ሳደርግ፥ ይኽ በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር። እና "አጀብ!" ያሰኘኝም ይኼው ነበር።

በእርግጥ እንዳልዋሽ ያኽል፥ ከዚኽ ቀደም ረዥም ጉዞ ማድረጌን ማበል አልፈልግም። ስለውሃ ኃይልና ልማት ጥበብ - ማለትም ሃይድሮሊክስ ለማጥናት ክፍለ አህጉራት አቆራርጦ የአየር በረራ ወደ ባሕር ማዶ አድርጌአለኹ። ግና ያ ሌላ፥ ይኼ ሌላ! የፊተኛው የጢየራ፥ይኼኛው በማኪና። እና በአገር ቤት ደረጃ - ክፍላተ ሀገር ዘለቅና ረዥም የመኪና ጉዞ ሳደርግ፥ ይኼ የመጀመሪያዬ ነው ለማለት ነው።

አስቀድሞ ግን "ይኽን ያኽል ማዳነቅ ከየት ተፈጠረብኽ?" የሚለኝ አይጠፋ ይኾናል። ቀልጠፍ ብዬ ልመልሰውና - ምናልባት ምናልባት - ያዲሳባ ልጅነቴ ሊኾን ይችላል። ከዚኽ ባለፈው ግን፥ ጉዞው በአጠቃላይ ከፈጠረብኝ ልዩ ስሜት በመነጨ መኾኑን አንባቢዬ በቅንነት እንዲረዳልኝ እፈልጋለኹ። አኹንም "እንዴት?" ባይ ካለኝ፥ ያው እንዳልኩት ንክር አዲሳቤ ነኝ። እና በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች - እሱም በተመጠነ ርቀት - ካዲሳባ ቢሾፍቱ፥ በሰሜን ምዕራብ - ከደብረሊባኖስ፥ በሰሜን ምሥራቅ ደግሞ ከደብረብርሃን አልፌ ማላቅ ያራዳ ጉልት ነኝ። ያኹኑን ዕድል ልበለው - ሎተሪ ወይም አጋጣሚ ወይም የሥራ ግዴታ የፈጠረው - ጉዞዬ፥ ከፊል ደብረ ኢትዮጵያን ያካተተ ነበር። ማለትም ሰሜን ኢትዮጵያን - ከአዲስ አበባ - ባሕር ዳር - ጎንደር - አክሱም - አዲግራት - መቐለ - ደሴን አቆራርጦ፥ አገሩን "አጀብ!" እያሉ አዲሳባ ከች! ባጭሩ፥

ይኼው ገጠመኜ - ልጆቹ እንደሚሉቱ - "ወይ ታሪክ! ወይ ጂኦግራፊ!" ነው ያሰኘኝ። ሌላም፥ሌላም!!

ወይ ሰሜን ኢትዮጵያ !?! ይቅርታ! አስቀድሞ ራሴን ማስተዋወቅ ነበረብኝ መሰለኝ። አዎ! በመጀመሪያ፥ ያዲሳባ ልጅ ነኝ ብያለኹ። ኹለተኛ፥ ሠራተኛ - የውሃ ሀብት ልማት ሚኒስቴር ባልደረባ። የሥራ ክፍሌም በሸለቆዎች ጥናት ሥር ነው። በሙያዬ - መሀንዲስ - ከመሀንዲስም የውሀ መሀንዲስ ነኝ። ሥልጠናዬ በኹለት ዘርፍ ነው። የመጀመሪያ ዲግሪዬን በሲቪል ምህንድስና ያገኘኹ ሲኾን፥ ኹለተኛውን ደግሞ በውሃ ምህንድስና ነው። ባጭሩ፥ ሃይድሮሎጂስት ነኝ። ከዚኽ በስተቀረ፥ በዝንባሌዬ - ሙዚቃ ማድመጥ፥ንባብና ጥናታዊ ፊልሞች ማየት እወዳለኹ። ንፋስና እሳት በጣም የምፈራ ሲኾን፥ ሰው፥መሬትና ውሃ ደግሞ ባም በጣም እወዳለኹ። ራሴን ለማስተዋወቅ ያኽል፥ ይኼ በቂ ይመስለኛል።

እና ያ በአድናቆት የተዋጥኩበት ጉዞ - ቀላል፥ አዛናኝና የሽርሽር ጉዞ አልነበረም። ለፕሮጀክት ጥናት፥ ሁለገብ የባለሙያዎች ቡድን ያሰባሰበ አድካሚ የሥራ ጉዞ ነበር። "እናስ?" የሚለኝ አይጠፋ ይኾናል። በጀ! ይኽቺ አጭር ማስታወሻ፥ ስለጉዞዬ የሥራ ራፖር እንዳይደለችና አንባቢዬንም በዚኽ መሰል ጉዳይ እንደማልደፍረው ይታወቅልኝ። ያው እንዲኽ ዐይነቱ ጉዳይ ከቅርብ አለቃዬ ጋር የሚያልቅ ነገር ነውና። ነገሬ ወዲኽ ነው። የጉዞው ድካም ከለቀቀኝ በኂላ፥ ጉዞው የፈጠረብኝን ልዩ ልዩ ትዝታ፥ ለአንባቢ የማካፈል ጉጉት አላስቀምጥ ስላለኝ ነው። እናስ? "የብቻ ትዝብቴን እነኾ!!" ለማለት ነው። እና እንደሥራ ከፊል ረቂቅ ሪፖርት ሳይኾን፥ በጎ ፈቃዳችኹ ኾኖ - እንደ አንድ ሀገረኛ ቱሪስት ይፋዊ ትዝብት አድርጋችኹ ቁጠሩልኝ።

ምናልባት ግን አኹንም "ምነዋ እንደ ቱሪስት ትዝብት?!" የሚለኝም አይጠፋ ይኾናል። ብርቱ ጠያቂ ካለ ደግ ! አንደኛ፥ ሰሜን ኢትዮጵያን ገና እንዳዲስ እንግዳ በማየቴ፥ ራሴን ከቱሪስት እኩል ቆጠርኩት። ኹለተኛ፥ ከሃይድሮሊክስ ባለሙያነቴ፥ ከሥራ ግዳጄና ኃላፊነት ባሻገር - ማለትም አብሮኝ ከኼደው ቡድን ቅኝት መኻል፥ ይኽ የኔ የነጠላው ሰው ግለኛ ትዝብት በመኾኑ ነው። እይታና ቅኝቴም ቱሪስት አከል በመኾኑ ነው።

እና አነሳሴ፥ ቢያንስ ቢያንስ ገና እንደ እንግዳ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ "በቱሪስት ዓይኔ" ስለቃኘኺቸው የሀገሬ ሰሜናዊ ክፍሎች ያደሩብኝን አንዳንድ ግለኛ ትዝብቶቼን ባካፍላችኹ አያጎዳም ብዬ ነው። "ምን አሳሰበኽ?" እባል ይኾን? እንጃ! ከኾነም፥ ይኽ ደግሞ አንድ ፊደል የቆጠረ፥ "የሠለጠነ" እና "የተማረ ሰው" የሚባል ሰው ኹላ አንድ አነስተኛ ተግባር ነው። እና እንኳን እኔ አንድ ነጠላው ዜጋ፥ የሀገሬ ተጓዥ ኹሉ፥ ሲኾንም ባለሙያ እንዲኽ ዓይነት የጉዞ "ሚምዋር" ቢኖረው አጥብቄ የምመኝ ሰው ነኝ። ይኼ ቢኾን ስለሀገራችን መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ፥ ስለተፈጥሮ ሀብት ይዞታችን፥ ሰለሕዝባችን ልዩ ልዩ የአኗኗር ደረጃ፥ ስለሀገራችን ዕድገት ኹኔታ ስንት ጠቃሚ የባለሙያ የልማት መረጃዎች እንለዋወጥ ነበር?! የሚል ጉጉቴ ብርቱ ነው። ባጭሩ፥ ይኽቺ ሙከራዬ፥ ከዚኹ ወሰን የለሽ ምኞቴ ወይም ቁጭቴ መኻል ቅንጣቲቱ ናት። ቢያንስ ፥ የዚኹኑ በጎ ምኞቴን አንዷት ጠጠር እንኳ ልወርውር ማለት ነው። እና አድናቆት ያነሣሣው ብርቱ ስሜት ካስጫረኝ በላይ፥ በአንድ ፊት (ምሁራዊ) የሞራል

ግዴታም ጭምር ገፋፍቶ - እነኾ እርሳስ አስጨብጦኛልና ይልቅስ “ትዝብትኽ ምንድነው?” ብባል፡፡ እና “እጅኽ ከምን?” በሉኝ፡፡

************

እንግዲያው፥ የመጀመሪያው አድናቆቴ የነቃው፥ ከአዲስ አበባ ሰሜን የሱሉልታን ጋራ ወጥተን - ጫንጮ- ሙከጡሪ - ፍቼ - ደብረ ጽጌን ከዘለቅን በኋላ 157ኛው ኪሎ ሜትር ገደማ ላይ የተገጣጠምነው የአባይ ሸለቆ ነበር፡፡ እግዚኦ ዓባይ!!! “ሳያዩኽ ያመኑ ብጹዓን ናቸው!“ ነበር ያሰኘኝ፡፡ ከኤለመንተሪ ክፍሎች አንስቶ ከትምህርት ቤት ደጃፍ እስክንሰናበት ድረስ - ስለኢትዮጵ ተራራማ፥ ሸንተራራማ፥በረሃማ፥ሜዳማና ሸለቆአማ መልክአምድራዊ ገጽታ፥ በሐተታ ዘኢትዮጵያ ጂኦግራፊ ጆሮ ጠገብና የካርታ ዓይን አዋጅ ከነበረ የዋኽ አስተያቴ “ደኽና ሰንብት!” ተባብለን የተቆራረጥነው፥ ከገሀዱ የአባይ ሸለቆ ጋር በውን በተገጣጠምንበት ቅጽበት ነበር፡፡ ስለኢትዮጵያ ፊዚካል ጂኦግራፊ - የልጅነት ምናቤ - አባይ ሸለቆ አፈፍ -ድንግልናው ተወሰደ፡፡

ከዚኽ ወዲያማ - መኪናችን ቀስ እያለ ወደ ሸለቆው እንብርት እያዘቀዘቀ ሲወርድ፥ ሦስት ድንገተኛና ውለኛ ስሜቶች ተፈራረቁብኝ፡፡ አንዱ፥ በዚያው በጉዞኣችን ሰሞን -ኅዳር 1987 ማለት ነው - በኢትዮጵያ ሬዲዮ በ “መጻሕፍት ዓለም” ፕሮግራም ሲተረኩ የነበሩት የሐዲስ ዓለማየኹ የ“ፍቅር እስከ መቃብር” ነፍሳት - የበዛብኽና የሰብለወንጌል የአባይ ሸለቆ መከራቸው ነበር፡፡ መኪና በሌለበት በዚያ በዚያ “የብጹዓን ዘመን” ይኽን መዓተኛ የአባይ ሸለቆ እንዴት እንደዘለቁት እንደጉድ አሳሰበኝ፡፡

ኹለተኛው፥ የሀገሬ ባለአገር ኹሉ፥ ስለአባይ - በዘመናት ሙሉ ያቀነቀነው አገር ሙሉ እንጉርጉሮ እንደተአምር ገኖ ተሰማኝ፡፡ እሱ ብቻ ሳይኾን፥ ውዳሴም ኾነ መርገም፥ ስለዐባይ ምን ያልተዜመ፥ ምን ያልተዘፈነ አለ? ምን ያልተባለ፥ ምን ያልታተተ አለ?!?

| | |
|---|---|
| አባይ የምድር ዓለም ሲሳይ | ከሜምፊስ እስከ ሜሮኤ |
| የቅድመ ጠቢባን አዋይ | በሥልጣኔ ትንሣኤ |
| አባይ የጥቁር ዘር ብሥራት | ከዴልታ እስከ ዴር ሡልጣን |
| የኢትዮጵያ ደም የኩሽ እናት | ከኡሙ-ራህ እስከ ኡሙ-ዱርማን |
| የዓለም ሥልጣኔ ምስማክ | አባይ የአቴስ የጡቶች ግት |
| ከጣና በር እስከ ካርናክ | ለዓለም የሥልጣኔ እምብርት |
| ……………………… | ጥቁር አባይ የጥቁር ምንጭ |
| አባይ የምድረ ኩሽ መኩሪያ | የካም ሥልጣኔ ፍንጭ |
| ከደምቢያ እስከ ኑ-ቢያ | ………………………… |
| ……………………. | |

……………………………

አባይ- አቢይ- አባይ ግዮን

ከምንጩ የጥበብ ሳሎን

ግሪክ ፋርስና ባቢሎን

ጭረው በቀዱበት ሰሞን

አባይ የአማልክት አንቀልባ

የቤተ ጥበባት አምባ

………………

በጥበብህ ሥርወ ፋና

አንቅተህ ባንቀልባ አዝለህ የቅድመ ታሪክን ዝና

የራምሴን አበ- ሲምቦል የመነሽን ልዕልና

በአልፋ የአልሙጋን ሐውልት፥ የቢያ ሐንኬን ፍልስፍና

በኮማምቦ የሰቦቃን፥ በናፓታም የኤዛና

ፊላኤ የአቴስን ምኩራብ፥ በልቅጾር የአሞንን ዜና

አባይ ታላቅ ቅድመ- ተስፋ

የኪነት ጉባኤ አልፋ

………………………

የቅድመ ጠቢባን አዋይ

አባይ የምድር ዓለም ሲሳይ

……………………………

እንኳን የሀገሬው ተወላጅ የሀበሻው ልጅ (ሎሬት ጸጋዬ ገብረመድኅን ቀዌሳ) ቀርቶ፥ የሰው ባዕዱ፥ የሰው ጥቁሩ፥ የሰው ቀዩ፥የሰው ነጩ፥ ቢጫው ሳይቀር - ስለአባይ ያለው ዝክር ምን ወሰን አለው? ያን ኹሉ በዓይነ ሕሊናዬ ልመዝነው ሞከርኩ፡፡

ሦስተኛው፥ ኹለቱን ስሜቶች ዘልቆ ያደመ መሰለኝ፡፡ ያው - በዚያ ቁልቁል ሸለቆ ውስጥ፥ ደጋግሞ እንደ ገደል ማሚቶ ያስተጋባባብኝ፥ የጸጋዬ ገብረመድኅን የጠነነ የ"አባይ" ቅኔው ነበር፡፡

የቅድመ ጠቢባን አዋይ

አባይ የምድር ዓለም ሲሳይ

በሕሊናዬ ሰሌዳ ላይ፥ ምናብና እውነታ እንዲኽ የምር ተፋጠው ነበር - ከሸለቆው እንብርት የደረስነው፡፡ "ወይ ተአምር!" አልኩ፡፡ እውነትም ያ የተመለከበት፥ ያ የተዜመ የተዘፈነለት፥ ያ የተነገረለት ዓባይ ……እግዚኦ የሸለቆው ጥልቀት!!! ከኪሎ ሜትር በላይ ቁልቁል እንጦርጦስ! የተፋሰሱ ስፋት! 70 ማይል ገደማ ነው አሉ፡፡ አጀብ! መልክአ ምድራዊ ግርማው! በጠቅላላው ዝም አሰኘኝ፡፡ ዝምታዬን ግን ወዲያው በሳቅ የፈታው፥ እፍኙ የአዲስ አበባ ውሃ ትውስታዬ ነበር፡፡ "ያዲሳባ ቀርሣ፥ያዲሳባ ግንፍሌ፥ ያዲሳባ ቁርጥሜ፥ የዲሳባ ቡልቡላ፥ ያዲሳባ ቀበና፥ያዲሳባ አቃቂ፥…..ቂቂቂ አፍራችኹ ሙቱ!!!" አሰኘኝ፡፡

ልክ ከዓባይ ድልድይ ስንደርስ፥ በጉጉት ከመኪና ወረድን፡፡ ድንቅ - ድንቅ ድልድይ! ከሙያዬ ተጽእኖ ይኹን አይኹን እንጃ፥ ፈጥኖ ትኩረቴን የሳበው ይኸው አጀብ የሚያሰኝ የአባይ ድልድይ ነበር፡፡ ከላይ ድልድዩ፥ ከታች ደግሞ ሸለቆውና የዓባይ ውሃ! ምኑን ልንገራችኹ?! ይኸ ትዕይንት፥ ውስጤ መንታ ነፍስ ዘራ ማለት ይቀለኛል፡፡

አዎ! ድልድዩን ሳስተውል፥ የግንባታው ጥበብ - ከተራ አድናቂነት በላይ የሲቪል ምህንድስና ትምህርቴን ቀሰቀሰብኝ። በግንባታው የመሳተፍ ዕድል ባያጋጥመኝም፥ በሀገሬ ምድር ላይ፥ በዚያ ጉደኛ ምድረ ፋይድ ሸለቆ ላይ የተንጠለጠለ፥ ያን ያኽል ረዥምና ግዙፍ ድልድይ ላይ፥ ማንም ይሥራው ማን - በሙያ ወገኖቼ ኮራኹ። ያን "የግብጽ ሕይወት" የተሰኘና የኛን ባካናና አይደፈሬ ዓባይ፥ እዚኽ ጋ በሲቪል ምህንድስና እንዲኽ አስገብረነው ሳስተውል፥ ልዩ ደስታና ሐሴት ወረረኝ።

የውሃው ነገር ደግሞ  አይወራ! ከድልድዩ ቁልቁል ሸለቆ ላይ፥  ያ ልዩ የደስታና የሐሴት ስሜቴ፥ ድንገት ደፈረሰ። "የውሃ ዛር ይኾን?" አልኩ። አዎ! ቡናማው የአባይ ድፍርስ ውሃ! እና ሳላስበው እልፍ ሐሳብ ወረረኝ። የዓባይ አምልኮ፥ የዓባይ ጂኦግራፊ፥ የዓባይ ታሪክ፥ የዓባይ ውሃ ፖለቲካ፥ የዓባይ ሥነ ጥበባት፥የዓባይ ሕይወትነት ወዘተ....ስንቱ?!! "እግዚኦ!" አልኩኝ - ብቻዬን እንደቀፈፈ።

ኋላ ውሃውን እያየኹ - ከዚያ ንክ ሐሳቤ ስሰክን፥ የውሃ ባለሙያነቴ ነፍስ ገዛ። ትዝታ ይኹን ሐዘን አልገባኝም። በመጀመሪያ፥ ሐሳቤ ፈጥኖ- በእግረ ኅሊና ባሕር ማዶ ወሰደኝ። ስለውሃ ኃይልና ልማት ጥበብ - ሃይድሮሊክስ ያጠናኹበት አውሮፓ፥ በዐይነ ኅሊናዬ ድቅን አለብኝ። ይኼኔ፥ የኾነ መራር የቁጭት ስሜት አንኀላጀኝ። እኔ በውሃ ጥበብ የሠለጠንኩባት አውሮፓ፥ የዛሬው የምዕራቡ ዓለም ሥልጣኔ እንብርት ናት። የአውሮፓ ሥልጣኔ መሠረት ግን የሮማ ሥልጣኔ ነበር። የሮማ ሥልጣኔ መሠረት ደግሞ የግሪክ ሥልጣኔ። የዚያ የግሪክ ሥልጣኔ ምንጭ ግን፥ ያ "የግብጽ ሕይወት" ፥ "የግብጽ ስጦታ" የተባለው የናይል ሥልጣኔ ነበር። ታዲያ "የዓባይን ልጅ ውሃ ጠማው!" ማለት፥ ከዚኽ ሌላ ምን ሊኾን ይችላል? ያ በዘመኑ ከጋንጀስ፥ ከኢንደስ፥ ከኤፍራጥስና ጤግሮስ ሥልጣኔዎች አቻና እንዲያውም ተወዳዳሪ የለሽ የነበረ ሥልጣኔ ምንጭና ባለሀብቶች - እኛ የዓባይ ልጆች - እነኾ ዛሬ እንኳን ውሃውን ልንጠቀምበት፥ ስለውሃው ነጋሪ ፍለጋ (አዎ!በሥልጠና ስም) አውሮፓ እንዳክራለን! የቁጭቴ ምሬት፥ የኾነ መራራ ሐሞት በሠራ አካላቴ አፈሰሰብኝ። እና ያን ውስጤ ታም ሊያፈነዳኝ የደረሰ የሐዘን ስሜት ማዕበል፥ የሸለቆው ገደል ማሚቶ ነፍስ ዘርቶ፥ እዚያው አምባው ላይ በእሪታ እንዲያስተጋባልኝ ተመኘኹ። አዎ! እንዲኽ እንዲኽ እያሰኘ.......

የመጽሐፈ ሙታን ዜና
ቋንቋ ለቋንቋ ቢራቀቅ

አድርጎህ ቅድመ -ገናና
የቅድሚያ ንድፍ ላይፋቅ

ዛሬ ወራቱ ራቀና
እዚህ ደማም እዚያ ተማም

ምድረ ዓለም ያንተን አድናቆት
መባልህ ብቻ ባይበቃም

ፈለጉን መሻት ተስኖት
የቅርስህ ጭብጥ ይዞታ

እንዲህ ባንተ መንከራተት
ሆኄታህ እስካልተፈታ

ታሪክ ወሮታህ ጠፍቶበት
አባይ! ፋናህ የህልም ርቅ

ትናንት በባዕድ ጨኽት
ፈለግህም ቢሆን ደቂቅ

ዛሬም ባላዋቂ ሁከት
ካልደረስንበት ፈልፍለን

እንዴት እንዴት ነበር ብለን
የጥንቱ አባይ እንዴት ትሆን?

አባይ - አቢይ - አባይ ግዮን!

“ይኸ ሐዘኔታ ያጣለቀው ቁጭቴ ምክንያታዊ ነው? አይደለም?” በሚል የጸጸት ስሜት ግን ወዲያውኑ ራሴን ቀጠቀጥኩት። ኾኖም ኋላ “ይኸም ሲያንሰው ነው!” ብዬ ተጽናናኹ።

ትክክል የማይኾነው፥ ባይቆጨኝ ነበር እንጂ! በውሃ ባለሙያነቴ እንደማውቀውና እንደሀገራችን የውሃ ባለሙያዎችም እምነት፥ በዓለም ላይ በውሃ ሀብት ባለጸጋ ናቸው ከሚባሉት አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ናት። ባለሙያዎቻችን እንዳመኑበት፥ በኢትዮጵያ መልክአ ምድር ላይ ከሚገኘው ጠቅላላ የውሃ ሀብት፥ 3 ቢሊዮን ሄክታር መሬት በመስኖ ማልማት እንደሚቻል ይነገራል። ይኹንና እስካኹን በአገር አቀፍ ደረጃ፥ ከ100 ሺህ ሄክታር በላይ አላለማንም። በኃይል ምንጭም ቢኾን፥ ባለን የውሃ ሀብት ወደ 60 ቢሊዮን ኪሎዋት በሰዓት - የኤሌትሪክ ኃይል ማመንጨት እንደሚቻል ይታመናል። ኾኖም እስካኹን በሰዓት ወደ 1.5 ሚሊዮን ኪሎዋት ገደማ ብቻ ነው ማመንጨት የቻልነው። በከተማና በገጠር ከሚኖረው ጠቅላላ የሀገራችን ሕዝብ መኻልም እስካኹን ከ20 ከመቶው በታች ብቻ ነው - ንጹሕ የመጠጥ ውሃ ማግኘት የቻለው። በውሃ ልማት አግጣጫ የትኛው ዳርቻ ላይ እንዳለን የሚያጠያይቅ አይደለም። እና ከዜግነት መቆርቆሬ በላይ፥ እንደ የውሃ ባለሙያነቴ፥ ገና በልማት ጎዳና ላይ እንኳ እንዳልገባን ስረዳ፥ ቁጭትና መንደዱ አያንስብኝም። ያውም ዓባይ ሸለቆ እንብርት ላይ ቆሜ!?!

በዚኽ ኹኔታ ዓባይ ድልድይ ላይ የቆየነው ለ15 ደቂቃ ነበር። የወረድነውን የሸለቆውን ቁልቁለት ያኽል፥ መልሰን አቀበቱን ለመውጣት ከመኪናችን ተሳፈርን። ድልድዩን በቀስታ ተሻግረን፥ ተዳፋቱን ሽቅብ ስንጀምርም፥ የአባይን የልማት በረከት እያውጠነጠንኩ ነበር። ይኼኔ ፥ ከቆየ የተማሪነት ትዝታዬ መኻል፥ አንድ ጉልኽ ትውስታ ፈገግ አደረገኝ።

ወቸ ጉድ!!! ነገሩ ይኸ ነበር። ገና የምህንድስና ተማሪ ሳልኾን፥ በኹለተኛ ደረጃ እያለኹ ነበር። 1964 ዐ.ም ገደማ ማለት ነው። ራሴን ማሞገስ ባይኾንብኝ....ብዙ ነገር ላይ ንቁ ነበርኩኝ። እና ከዚያን ወቅት ትውስታዬ፥ ስለዓባይ ልማት የተደረገ አንድ ማራኪ ሐሳብ ውል አለኝ። ዓባይን ለመስኖና ለኤሌትሪክ ኃይል ልማት ለማዋል የ“ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ሪክላሜሽን ቢሮ” በያኔው የኢትዮጵያ ብር ወደ ኻያ ሚሊዮን ገደማ ወጪ አፍሶ ያደረገው ጥናት ዜና ትዝ አለኝ። ምናልባትም ወደ ምህንድስና ሙያ የመራኝ ረቂቅ ፍላጎት የሠረጸብኝ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እንዳልቀረ እገምታለኹ። እና እንደማስታውሰው - በዓባይ ተፋሰስ ዙሪያ ብቻ ወደ 33 የሚጠጉ ልዩ ልዩ የልማት ፕሮጀክቶችን ማከናወን እንደሚቻልና የመጀመሪያ ደረጃ ጥናቶችም መጠናቀቃቸው መገለጹም አይረሳኝም። ይኸውም የጥናት እቅድ 4 ትላልቅ የመስኖ ግድቦችን ይጨምራል ተብሎ መዘገቡም ይታወሰኛል። እና በእኒኽ ግድቦችም - በያኔው የሕዝብ ቆጠራ ግምት፥ በዓባይ ተፋሰስ ዙሪያ ለነበሩቱ 4 ሚሊዮን አርሶ አደሮች ታላቅ የልማት ተአምር መፍጠር እንደሚቻል ተነግሮ ነበር። ባልዘነጋ... ወደ 50ሺህ ሄክታር መሬት በመስኖ

በማልማትና በውሃ ኃይልም አቅጣጫ - በሰዓት በአማካይ ወደ 173 ቢሊዮን ኪሎዋት የኤሌትሪክ ኃይል ማመንጨት እንደሚቻል፥ ትልቅ ተስፋ ተነግሮ ነበር። በዚኽ ቅጽበት፥ እዚኽ ዓባይ ሸለቆ አቀበት ላይ፥ ያ ማራኪ የልማት ጥናትና ውጥን እንደ ጉድ ድቅን አለብኝ። የያኔው የስሚ ስሚዬ ደግሞ የዓባይን ፕሮጀክት ጥናቶች ኢትዮጵያ በሥራ ላይ ለማዋል ብትሻ፥ የበጀቱ ነገር አቀበት በአቀበት መገመቱም አንዱ ነገር ነበር - የያኔውን የኢትዮጵያ የ18 ዓመት በጀት ይጠይቃል መባሉ!! ምናልባት ከዚያ ወዲኽ አንድ ተጨባጭና አንድ ለእናቱ ፕሮጀክት የፊንጫአ ግድብ ነው። በዚኹ መነሾም አቀበቱን በጥንቃቄ እየወጣጣን " ዛሬ የዓባይ ፕሮጀክት የያዛቸው መረጃዎችና ውጥኖቹ ምን ምን ይኾኑ?! " ብዬም አሰብኩ።

ወዲያውኑም ቀድሞ ትዝ ያለኝ፥ የልብነ ድንግሉ እንግዳ ሰው - ፖርቹጋላዊው ፍራንሲስ አልቫሬጽ ነው። እና በበረሀው ንዳድ እየቃተትኩ "ይኼ አልቫሬጽ የኔን መሰሉን - የስንቱን ተጓዥ ትኩሳት ተወጥቶት ይኾን?" አሰኘኝ። ብቻ አልቫሬጽን አሰብኩት። ምንም እንኳ ከአልቫሬጽ አንድ መቶ ዓመት በኋላ፥ ሌላው የአገሩ ሰው እውቁ ጀዝዊት ሚሽነሪ ጀሮሜ ሎቦ፥ ስለዓባይ በጻፋቸው አይረሴ ማስታወሻዎቹ አውሮፓን ያስደነቀ ቢኾንም፥ ግን ማን እንደ አልቫሬጽ?! አልቫሬጽ ኢትዮጵያ የደረሰው እ.ኤ.አ ወደ 1520 ገደማ ነበር። በዚያ ጨለማ ዘመን - "የካህኑን ዮሐንስ አገር" -ይኽችን ምድረ አበሻና የታላቁን ግዮን ምንጭ በታሪክ ናፍቆት ተጎትቶ በብርቱ ስሜት ከመጣ በኋላ፥ በምዕራብ ኢትዮጵያ የዓባይ ሸለቆዎች ዙሪያ 6 ዓመታት ያኽል ባዝኗል። እና እንግዳ በኾነ ዜና መዋዕሉ፥ ስለዓባይ ለአውሮፓ ቀድሞ ያበሰረ አልቫሬጽ ነው። እና ዓባይ ሸለቆ በረሀ ላይ እንዲኽ እየባዘንኩ፥ አልቫሬጽን አለማሰብ እንዴት ይቻለኛል?

ሌላው ደግሞ፥ እኔው ራሴ "የዓባይ ጀግና" ብዬ ስለሰየምኩት ሰውዬ! አዎ! በአልጀርስ የእንግሊዝ ቆንሲላ የነበረ፥ ያ የወይን ነጋዴ፥ የሕግ ባለሙያና አገር አሳሹ እስኮትንላዳዊ ጀምስ ብሩስ። ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረው እ.ኤ.አ በ1769 ገደማ ነበር። የዓባይን ምንጭ ፍለጋ ማን እንደሱ የወጣና የወረደ፥ የማሰነና የዳከረ አለ? በምዕራብ ኢትዮጵያ የዓባይ ተፋሰስ ዙሪያ በፍቅር ተንከራትቷል። እና አገሩ ሲመለስ፥ እንደ አልቫሬጽ ኹሉ ለአውሮፓውን ብቻ ሳይኾን፥ የዓባይን ዝና ለዓለም ጭምር የነዛ - ዝግና ዘዓባይ ነበር። እና አኹንም ዓባይ በረሀ ላይ ጀምስ ብሩስን ያኽል ሰው እንዴት ማስታወስ ያንስብኛል?! እና ይኽ "የዓባይ ሰማዕት" ስለ ዓባይ ውሃ ዝና፥ ስለምንጩ፥ ስለተፋሰሱ ዙሪያ፥ ስለዓባይ ሰዎች ጠባይና አኗኗር ወዘተ....ብቻ 5 ቅጽ ዳጎሳ መጻሕፍት የጻፈ ጉደኛ ሰው ነው። ምንም እንኳ፥ የኋላ የኋላ የአገሩ ልጆችና እውቆቹ የዓባይ አሳሾች እነዴቪድ ብሩስ፥ እነሳሙኤል ቤከር፥ እነአላን ሙርሄድና ቼዝማን ወዘተ.... ስለዓባይ የሚያባብሉ ማስታወሻዎች መጻፋቸው ቢዳነቅም፥ ግን እንደመጀመሪያውና እንደበኩሩ ጀምስ ብሩስ ማን ቀዳሚ ሊኾን ይችላል? እና ከዓባይ አሳሾች ኹላ፥ ሕሊናዬ በዚኽ ቅጽበት አግኖ ያደነቀው - አልቫሬጽና ጀምስ ብሩስን ነበር።

የታሪክ ትውስታ በእኒኽ በኹለቱ የዓባይ ጀግኖች የታሪክ ትዝታ ጠለፈኝ እንጂ፥ ካነሳኹት ከዓባይ ፕሮጀክት ሰዎች ጋር ትዝብት የሚያጣጥለኝም ነገር ነበር። ይኹንና ይኼ ትውስ ያለኝ ኋላ ነው። "የክፍለ ዘመናችን ኹለት ድንቅ የዓባይ አሳሾችን በመዘንጋቴ ቅር ሊሰኙ ይችሉ ይኾናል" አልኩ - ልክ ሐሳቤ ኹሉ ውጪ የተጋለጠ ይመስል። ኋላ አደብ ገዝቼ "አዎ! ማን እንደነሱ!?" አልኩ። በፈረንጆቹ 1960 መግቢያና መጀመሪያ ገደማ፥ ስለዓባይ ሸለቆ ልማት ሰፊ

ጥናት ያደረገው የዚያ "የዩናይትድ ስቴትስ ሪክላሜሽን ቢሮ" ባልደረባና የመስክ ኢንጂነሩን ሊል ሞቦትን የሚያኽል ማንም ሊኖር አይችልም።

ለካ የዓባይ በረሀ፥ የዓባይ አዚም በቀላሉ የሚለቅ አልነበረም። ደግሞ ሌላ ድንገተኛ ትውስታ ጠለፈኝ። አንዳንዴ አይታሰብ የለ - በዘመናት ዕድሜ ውስጥ ያለፉ፥ "የዓባይ ሕልመኞች" እና "የዓባይ አሳሾች" ድንገት ትውስ አሉኝ። ኋላ ሳጤነው - "ግን በዓባይ ነገር ተማርኮ፥ ባሕር ማዶን ቆርጦ የመጣን ስንቱን ተጓዥ፥ ስንቱን ነጋዴ፥ ስንቱን ሚሽነሪ፥ ስንቱን ዲፕሎማት ነቅሼ እችላለኹ?" አሰኘኝ። አዎ! ዓባይን እኮ እንኳን ተራ የፈረንጅ ዜጋ ቀርቶ፥ ነገሥታቱ ጭምር እኮ ቋምጠውታል። "እና ሥፍር ቁጥር የሌለውን የዓባይ አሳሽ ማንሳቱን ባልሞክረው ይሻላል" አልኩ። ለምሳሌ፥ በአንድ በ16ኛው ክፍለ ዘመን፥ ከአውሮፓ - ከአንዲቱ ፖርቹጋል ብቻ ሮድሮጎ ዲ ሊማ፥ ፍራንሲስኮ አልቫሬጽ፥ ካስታን ኾዞ፥ ፔሮ ፓኤዝ፥ ማኖኤል ዲ አልሜይዳ፥ አንቶኒ ፈርናንዴዝ፥ ማኖኤል ባራዲስ፥ ወዘተ... ስንቱ ይቆጠራል? ይልቅስ ተራዎቹን ትቼ፥ የዓባይ ምኞታቸው በገሀድ ያጋለጣቸውን ጥቂቶቹን ነገሥታት መጥራት ይቀለኛል። ከጥንቶቹ ታላቁ እስክንደርና ጁሊየስ ቄሳር፥ ከመካከለኛው ዘመን የፖርቹጋሉ ዮሐንስ ዳግማዊ የእንግሊዙ ጆርጅ ሳልሣዊና የፈረንሣዩ ሉዊስ ዐሥራ አምስተኛ...!!! ይኹንና በዚኽ ሰዓት፥ የዓባይ ዳርቻን በብርቱ ጉጉት ካነፈነፉ አያሌ ጸጉረ ልውጦች መኻል - ድንገት ኹለቱን ብቻ ኅሊናዬ አደነቃቸው።

ያው ቀድሞ ትዝ ያለኝ....የአጼ ልብነድንግሉ እንግዳ ሰው.....ፖርቹጋላዊው ፍራንሲስ አልቫሬጽ !!!

ደግሞ እውቁን አሜሪካዊ ሊል ሞቦትን...!!! ደሞዬ.."ምነዋ እሱን ብቻ!?!.." የሚልም አጠይቆት ወዲያው ጠለፈኝሳ። ልክ ነበር። አዎ! ከፊትም ኾነ ከኋላ - ሞቦትንና ያን ተባባሪውን ኢትዮጵያዊ ኢንጂነር ደመቀ መኩሪያን ያኽል - ዓባይን ያሰሰ ማንም ሊኖር አይችልም። እኒኽ ኹለት የክፍለ ዘመናችን የጥቁር ዓባይ አሳሾች - ከዓባይ ምንጭ ተነስተው፥ ተፋሰሱ በሚያካልላቸው ሰባት የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገራት ዙሪያ እስከ ሱዳን ጠረፍ ድረስ የሸለቆውን ጓዳ ጎድጓዳ ያሰሱ ጎደኞች ናቸው። አምስት ዓመታት ሙሉ በሄሊኮፕተር 200 ሺህ ኪሎ ሜትር ካሬ በርሮ የአባይን ምሥጢር በመበዝበዝ አንዳችም ተወዳዳሪ የማይገኝላቸው "ብርቅዬ የዓባይ ልጆች!" ናቸው። እርግጥ ነው - በየጊዜው-በየመስኩ አብረዋቸው የነበሩቱን ሜትሮሎጂስቶች፥ ቀያሽ መሀንዲሶችና ረዳቶቻቸው፥ መካኒኮች፥ ምግብ አብሳዮቻቸው ሳይቀሩ ኹሉንም በአድናቆት አሰብኳቸው። አዎ! ግን ማን እንደሊል ሞቦትና እንደ ኢንጅነር ደመቀ መኩሪያ!?!....

ዘይገርም! ኋላ ላይ ደግሞ ፈገግ ያደረገኝ የሄሊኮፕተር አብራሪው ጉዳይ ነበር። "ምነው ክብሩን ለኹለቱ ብቻ ሰጠኹ? ብቻቸውን አልነበሩምና!" የሚል አባዜ ነበር። ሦስተኛውን ድንቅ ሰው ፍለጋ ገባኹ። ወዲያው ግን " ለመኾኑ ያን ኹሉ ጓዳ ጎድጓዳ የበረረ አንድ ወይስ ኹለት ሦስት አብራሪዎች በፍርርቅ አበሻ ወይስ የፈረንጅ አብራሪ ወይስ አብራሪዎች??!" የሚል ድንገተኛ ጥያቄ አቆመኝ። ፈጣኑ ምላሼም ሳቅ ኾነ። አንድም ይኹን ኹለት ሥስት - ብቻ ሦስተኛውን ብርቅ ወይም ብርቅዬ የዓባይ ሰው ወይም ሰዎች እወቁልኝ ባይ ነኝ።

ከምናባዊው የዓባይ ትዝታዬ የነቃኹት አቀበቱን አጋማሽ ላይ ስንደርስ ነበር፡፡ ይኼኔ ነበር - ከስሜታዊነት ወጥቼ፥ ከሙያዬ አንጻር ስለዓባይ ተጨባጭ ልማት በጥሞና ያሰላሰልኩት፡፡ “እንደበረኸኛ በደዊ ሀሩር ለሀሩር እየኼደ ‘ሌክቸር’ ብጤ ነገር ይዳዳዋል ወይ? ” አትበሉኝ እንጂ - የውሃ ልማት ሲታሰብ - ውሃ ውሃ የሚያሰኝ ስንት ነገር አለ መሰላችኹ?!

“ለአንበሳ አይመትሩም፥ ለብልህ አይነግሩም….” አይደል?….ኾኖም፥ የውሃን ነገር፥ የውሃን ልማት ጣጣ የኛን የባለሙያዎቹን ያኽል ችግሩን የሚረዳው ከስንት አንድ እንደኾነ መገመት አያቅትም፡፡ ኧረ ስንት መዓት ነገር አለ! አዎ! የመስኖን ልማት ለመዘርጋት፥ የኃይል ምንጭ ለማቋቋም፥ ወንዝ ገድቦም ኾነ ጉድጓድ ቆፍሮ ጥራቱ የተጠበቀ፥ መጠኑ አስተማማኝ የኾነ ንጹሕ የመጠጥ ውሃ ለሃገራችን ሕዝብ ለማዳረስ የሚደረገው ጥረት በዘፈቀደና በአጭር ወራት የሚከናወን ቀላል ተግባር አይደለም፡፡ ዓባይ ይኹን ተከዜ፥ ባሮ ይኹን ሸርሌ - በእያንዳንዱ ተፋሰስና በከርሰ ምድር የሚገኘውን የውሃ መጠን፥ ዓይነትና ሥርጭት - በየብስ፥ በአየርና በሳተላይት አማካኝነት ለረዥም ዓመታት ያለማቋረጥ መረጃ በማሰባሰብና በማከማቸት፥ በተለያዩ ዘዴዎች በኮምፒዩተር ጭምር በመተንተን፥ የተሟላ የውሃ ማስተር ፕላን የማዘጋጀት የትየለሌ የሥራ ድካም አለ፡፡ ይኽም የጂኦግራፊ፥ የጂኦሎጂ፥ የኤኮሎጂ፥ የሃይድሮሎጂ፥ የዲሞግራፊ፥ የሚቲዎሮሎጂ፥ የኢነርጂ፥ የምህንድስና፥ የኢኮኖሚክስና የሶስዮሎጂ ባለሙያዎችን የቡድን ጥረት በብርቱ የሚጠይቅ፥ መዓተኛ ተግባር ነው፡፡ እና ይኽን የማድረግ አቅም ሲኖረን ብቻ ነው - ያለንን የውሃ ሀብት ለሀገራችን ሕዝብ ብልጽግና ማዋል የምንችለው፡፡ ውጤትም የምናገኘው - ሀገራችን ተጨማሪ የውሃ ባለሙያዎችን አሠልጥና፥ ለዚኽ ዓይነተኛ የልማት ግብ ሙሉ በጎ ፈቃድ ያላቸው ሀገረኛ ባለሙያዎች ማደራጀት ስትችል ብቻ ነው፡፡ ጥሩ ዲስኩር ብጤ መሰለኝ! ለነገሩ፥ የአኹኑ ጉዞዬ ራሱ፥ የዚኹ ጥረት መቅድማዊ ዝግጅት በመኾኑ፥ አዎ! ስለዓባይ ልማት ባወራ አላፍርም፡፡ አዎ! ስለተከዜ፥ ስለዋቢ ሸበሌ፥ ስለኦሞ - ጊቤ እና ስለአዋሽ ልማት ባወራ ማይደካክመኝ ዓይነቱ ነኝ፡፡

ይልቅዬ - ኢትዮጵያውያን የውሃ ባለሙያዎቻችን እንደሚሉት፥ የሀገራችንን ተራራና ሸንተረሮች፥ ሜዳዎችና ሸለቆዎች ላይ የሚዘንመውን የዝናም ውሃ ወደተለያየና ተመሳሳይ አቅጣጫ አጠረቃቅመው የሚወርዱ ታላላቅ ጅረቶች 12 ናቸው፡፡ ከእኒኽም ታላላቅ የውሃ ፋሎች አንዱና ዋነኛው ታላቁ ጥቁር ዓባያችን ነው፡፡ ካቀበቱ ቁልቁል እያየኹት ነበር! እና ታዲያ እኒኽ 12 የሀገራችን ታላላቅ ወንዞች ወደ 111 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ ገደማ ያፈሳሉ፡፡ ከዚኽም ውስጥ በቀጥታ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል ተብሎ የሚገመተው፥ 97 ቢሊዮኑ ሜትር ኩብ ገደማ መኾኑን ይናገራሉ፡፡ ይኽ የውሃ ሀብታችንም፥ አፍሪካ አላት ከሚባለው 4ሺህ ቢሊዮን ሜትር ኩብ ጋር ሲነጻጸር 3 በመቶ ገደማ ነው፡፡

አንባቢዬ እንደኔ እንደኔ ከኾነ፥ እዚኽ ላይ የአባይን የልማት ድርሻ እግረ መንገዱን እንዲሚጠይቅ ልቤ እየነገረኝ ነው፡፡ ግምቴ ትክክል ከኾነም፥ የዘመኑ ብሂል ነውና በእስታትስቲክስ ባወራ ሚፈቅድልኝ ይመስለኛል፡፡ የኛ የኢትዮጵያውያን “ዓባያሎጂስቶች” እንደሚሉት “ በጥቅም ላይ ሊውል ይችላል ከምንለው የሀገራችን የውሃ መጠን ውስጥ፥ ከግማሽ በላይ ማለትም 53.2 በመቶው፥ በአንድ በዓባይ ተፋሰስ ውስጥ ውስጥ ተካቶ የሚገኝ ነው፡፡ የዓባይ ተፋሰስ ከአገሪቱ የቆዳ ስፋት 17.5 በመቶውን የሚያዳርስ ሲኾን፥ በዚኽ ተፋሰስ

የሚኖረው ሕዝብ ብዛትም ከጠቅላላው የሀገሪቱ ሕዝብ 27 በመቶ ያኽል ነው። በዚኽ አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያለው 27 በመቶው ያገራችን ሕዝብ፥ ከሀገሪቱ የተፋሰሶች ውሃ መጠን ከግማሽ በላይ የሚኾነው ይደርሰዋል ማለት ነው። "የውሃ ነገር ውሃ ያነሳል" እንበልና...ሌሎቹንም ትላልቅ ተፋሰሶች በዚኽ አጋጣሚ ብንደምራቸው - ማለትም ተከዜን፥ ኦሞን፥ ጊቤን፥ ባሮንና አኮቦን ብንጨምራቸው - ካገሪቱ የውሀ ሀብታችንን ይዘው ከጠቅላላው ሕዝባችን 44 በመቶ ለሚኾነው የልማት ተስፋ የሚኾኑ ናቸው።

ነገር ቆስቋሼ - የአበሻው ዓባይ ነውና እሱኑ አምርሬ ባማ ይሻላል። እንጂ ከኢኳቶሪያል ጋራዎች ሥር መንጭቶ፥ 2.9 ካሬ ኪሎ ሜትሮች በማካለል 10 የአፍሪካ አገሮችን አቆራርጦ፥ 6፣700 ኪሎ ሜትር በመጓዝ ለግብጽ ሕይወት የሚኾነው ታላቁ ናይልማ ጉዱ ብዙ ነው። እና ስለኛው ጥቁር ዓባይ ብቻ ማንሳቱ አይበጅ? አዎማ! ዓባይ በረሀ ላይ ....ምናልባት ከዓባይ ከራማ ጋር ለመታረቅ።

አጀብ ዓባይ?!!..."ነገርን ነገር ያነሳዋል!" ይልቅ በዚኽ የጉዞ አጋጣሚ፥ አንድ ሊዘነጋ የማይገባ ነገር ትውሽ አለኝ። ከዚኹ ጉዞዬ ቀደም ባለው ወር፥ የኛው የውሃ ልማት ሚኒስቴር "የዓባይ "ልጅ" በሚል ርእስ፥ በመስከረም 1987 ዐ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ፥ በተከታታይ ያወጣው ሐተታ ዘዓባይ ግሩም ምርምራዊ ጽሑፍ ታወሰኝ። ሕዝባችንን ስለዓባይ (ስለሌሎች ወንዞቻችንም) ልማት የሚያነቃቃ፥ ችግሮቹንም አጢኖ ሕዝባችን ለውሃው ልማት በቁርጠኝነት እንዲነሳሳ የሚጎተጉት በሳል ጥናታዊ ጽሑፍ ነበር። ታዲያ ከዚያ እሰዬ ከሚያሰኝ ትንተናዊ ጽሑፍ አንዳንድ ዋና ዋና ጉዳዮችን ለማስታወስ ሞከርኩ። .....ማስታዎሻዬን አገላበጥኩ።

*.....በዓባይ ተፋሰስ ውስጥ ያለውን ወቅታዊ የውሀ መጠን ብቻ ብንመለከት ከወንዙ ዓመታዊ ፍሰት ውስጥ ከ84 ከመቶ በላይ የሚኾነው ከሐምሌ እስከ ጥቅምት ድረስ ባሉት አራት ወራት የሚከሰት ነው። ከጊዜ አኳያ ሲታይ ሥርጭቱ የተዛባ እንደኾነ እንገነዘባለን። ችግሩ ይኼ ብቻ አይደለም። ከኢትዮጵያ ጠቅላላ የውሃ ሃብት ውስጥ ከ91 ከመቶው በላይ የሚኾነው ወደ ጎረቤት አገሮች የሚፈስ በመኾኑ አገራችንን ብቸኛ ተጠቃሚ አያደርጋትም። እንዲኽ እየተጋነነ የሚነገርለት የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት መጠን ከመልክአ ምድራዊና ከጊዜ አንጻር ሥርጭቱ የተዛባ ብቻ ሳይኾን፥ ወንዞቹ የወሰንና ወሰን ተሻጋሪ በመኾናቸው ውሃውን በሚገባ ለመጠቀም፥ ከሚጠይቀው ከፍተኛ የኢንቨስትመንት መጠን ሌላ፥ የውሃ ፖለቲካ ጉዳይ በቀላሉ የሚታለፍ አለመኾኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።...*

የዓባይ በረሀ ንዳድ ድንገት የጠወረኝ ይመስል - ሳላስበው እብደታዊ ሳቅ ሳቅኹ። ደግነቱ ይኽ ንክነት የመሰለ ነገሬ በመኪናው የአቀበት ሥቃይ ተሸፍኖልኝ፥ ከጎኔ ካለው የሥራ ባልደረባዬ ትዝብት ላመል ተረፍኩ።ግን፥ ምን መትረፍ ይሉታል? እንዲያውም፥ የለየለት የበረሀ ብዥታ ብለው ሳይሻል አይቀርም። እንደውሃ ምንድስና ባለሙያነቴ፥ ስለውሃ ሀብታችን መትረፍረፍና ስለልማቱ ደጋግሞ ያውጠነጥን የነበረ ኅሊናዬ፥ ድንገት በዚኽ ቅጽበት ከትክክለኛው እውነታ ጋር ሲፋጠጥ፥ እውነት እላችኋለኹ - ስሜቴ እንዳለፈው ሐምሌ የዓባይ ውሃ ብጥብጥ አለ። ከላይ የበረሀውን ሐሩራዊ ወላፈን፥ ከታች ደግሞ ያንኑ ጠቋራ ዓባይ ቁልቁል እያየኹ - ያ የውሃ ሀብታችን የምለው ነገር ኹሉ - "ተረት!ተረት!" ዓይነት "የሕልም ዣት" ያኽል ኾኖ ተሰማኝ። ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ልበለው ወይስ ንዴት ብጤ!? ብቻ በዚኹ መነሾ፥ የኾነ

ወፈፌ ሐሳብ ወረረኝ፡፡ "የውሃ መንገደኛ - የጅረት በደዊ - የወንዝ ዘላን ኹላ ይዘን - ምን የውሃ ሀብት፥ልማት…ቅብጥርጥሶ …ምን አሰኘን?" የሚል ሞገደኛ..መንገደኛ ስሜት ነበር፡፡ እና ይሰማኝ ይመስል - መልሼ ቁልቁል እያየኹት - ዓባይን በልቤ - "ከንቱ!ከንቱው ዓባይ!!!" አልኩት፡፡

"አዱኛ ብላሽ!" ማለት ከዚኽ ሌላ ምን ሊኾን ይችላል? ሳይታለም የተፈታ ነገር- ድንበራችንን ዘሎ ወደ ጎረቤት አገር የሚፈስ አንድ እብድ እና ጀብደኛ ጅረት ቢኖረን ይኼው ሞገደኛው ዓባይ ነው፡፡ በራሱ ቢያበቃ ደግ ነበር፡፡ ሌሎቹንም አግሮ፥ ሀገሪቱን ሙልጭ የውሃ ደሃ የማድረግ አዚም አለበት እንጂ! የዘመናዩቱ ግብጽ መጋቤ ሕይወት የኾነውን የአስዋኑን የናይል ግድብ ከርስ የሚሞሉት ዓባይን ጨምሮ አራት ትላልቅ ድንበር ዘለል ተፋሰሶቻችን ናቸው፡፡ እና ያ የውሃ ሀብታችን አዱኛ ገንዘቡ የሚያደርግ አብዩ አስዋን፥ በየዓመቱ በአማካይ ከሚያገኘው 84 ሚሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ ፍሰት ውስጥ፥ 72 ሚሊዮኑን ሜትር ኩብ ያኽል ወይም 86 በመቶውን ያኽል የሚገብሩለት፥ እኒኹ የሀብታም ደሃ የሚያደርጉን አንጋፋ (ገፋፋ ቢኗቸው ይመረጣል) ጅረቶች ናቸው፡፡

እና ከኢትዮጵያ ጠቅላላ የውሃ ሀብት ውስጥ 91 ከመቶው እጅ ወደ ሱዳንና ግብጽ ሾላኪ ነው፡፡ ቁጭት የሚያሳድር ነው፡፡ ዓባይን ከተዳፋቱ ሥር በርቀት አየሁት፡፡ "ቸሩ" እና "ለጋሱ" ዓባይ ዳርቻ ቆሜ፥ በሱዳንና በግብጽ ላይ የምቀኝነት ስሜት ማቀንቀኔ ትንሽ ሞራለ ቢስ ካስመሰለኝ ምን አረጋለኹ? ይኽ የሚያሳፍር ከኾነ፥ ማፈር ያለባቸው ዓባይና ጭፍሮቹ ናቸው፡፡ እና ገሚሱ የውሃ ሃብታችን በደቡብ ሱዳን - ሱድ በሚባለውና በዓለም ተወዳዳሪ የለውም በተሰኘው ረግረጋማ ቦታ ተንጣሎ በመተኛት በበጋው ንዳድ ተሰልቦ እንደጉድ ተኖ ይጠፋል፡፡ ገሚሱ ደግሞ በርክት ብሎት፥ ለግብጽ ሕይወት ይኾናል፡፡ ደርሶ ባገር ምን ውሃ አለ?!

ያለምንም ጥርጥር "ወይ ነዶ !" የሚያሰኝ ነው፡፡ ከእኒኽ ዱር አዳሪ ወንዞቻችን አንዱና ዋናው ዓባይ ነው፡፡ ኹለተኞቹ ተፋሰሶች - ጊሎ፥ ዲነዲርና ራሃድ ናቸው፡፡ ከኢትዮጵያ ድንበር ካለፉ በኋላ ሱዳን ላይ ከናይል ወንዝ ጋር ይቀላቀላሉ፡፡ ሦስተኞቹ፥ የተከዜ ተፋሰሶች ናቸው፡፡ በዚኽ አቅጣጫ ዋነኛው የተከዜ ወንዝ ሲኾን፥ አጋሮቹ ጉአንግና አንገረብ ናቸው፡፡ ሱዳን ውስጥ አትባራ ከተባለው ወንዝ ጋር ተገናኝተውሉ ከዋናው ናይል ጋር ይቀላቀሉ፡፡ አራተኞቹ፥ የባሮና የአኮቦ ወንዞች ናቸው፡፡ ከሱዳን ጋር ድንበር አካለው ከነጭ ናይል ጋር ይገናኛሉ፡፡…

ግን እስከ መቼ "ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል!"? ወይም እስከመቼ " የጨው ክምር ሲናድ ሞኝ ይስቃል!"? እኒኹ ዘላኖቹ - የኢትዮጵያ  የናይል ተፋሰሶች፥ ከአገሪቱ ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 42 ከመቶውን፥ ከጠቅላላው የሕዝብ ቁጥር 38 በመቶውን የሚሸፍኑ ሲኾን፥ በሀገሪቱ ሊለማ ይችላል ተብሎ ከተገመተው መስኖ 59 በመቶውን፥ ለኃይል ምንጭ ደግሞ ተስፋ ከተደረገው 64 በመቶውን ያኽል ሀብት የያዙ ናቸው፡፡ ወይም ባጭሩ፥ ለሀገራችን የመስኖ ልማትና ለኃይል ምንጭ እንዲኹም ለእንዱስትሪና ለመጠጥ ፍላጎታችን 80 ከመቶውን በላይ ያኽል የሚሸፍኑት እኒኽ ታላላቅ ተፋሰሶች ናቸው፡፡ እና "ሃይ!" ባይ ይገባቸዋል፡፡

ከቅድሙ የተስፋ መቁረጥ ስሜቴ ጋር ተቆራርጬ ስላለው እውነታ በመረዳት መኾን ስለሚገባው ነገር ማሰላሰል ያዝኩ፡፡ አዎ! ለባዶ ኩራት ካልኾነ እንጂ፥ ከአዋሽ በቀር አንድም

አገር አዳሪ ውሃ እንደሌለን አዳሜ ኹላ ቁርጡን ማወቅ አለበት" አልኩ። እንኳን ያ "የዓባይ ልጅ!" ጥናት እንኳን ምሥጢሩን ገለጠልን እንጂ፥ ከንቱ ዓባይና ጭፍሮቹ "በሕግ አምላክ!" ሊባሉ ይገባል። "ሃይ!" ለማለት፥ በእርግጥ የጥበብ አቅም እንደሚጠይቀን አመንኩ። አዎ! ቀላል አይደለም። የዕውቀትና የኢንቨስትመንት መንታ ክንድ ነው የሚጠይቀን። በዚኽ ላይ ሥሉስ የሚገባ ነገር ካለም አንድ ውለኛ ነገር ነው። ብርቱ የልማት ፍላጎትና አይበገሬ ብሔራዊ ስሜት ይፈልግብናል። እና ከሕዝባችን ያላሰለሰ ተነሳሽነትና የድርጊት ጥረት፥ ከእኛ የውሃ ባለሙያዎች ደግሞ የዕውቀት ልቀትና የአገልግሎት በጎ ፈቃደኝነት። የልማት ተስፋችን እውን የሚኾነው ይኽ እንደ ዓባይ የነሐሴ ውሃ ምሉዕ መኾን ሲቻል ብቻ ነው።…

ለካ የዓባይን ሽለቆ አቀበት እያገባደድን ኖሯል?! ዓባያዊውም ሽለቆ ሲጠናቀቅ፥ ለካ ሸዋም " ደኅና ሰንብት!" መባል ይኖርበታል። በዚኹ የፍጻሜ ቅጽበት " አይ ዓባይ!! ልማትኽ ገና ኾነ እንጂ፥ ምሥጢርህስ ተጋልጧል!" ብዬ፥ የልማቱን ተስፋ ለመጪዎቹ ጊዜ አደራ ሰጥቼ ሽለቆውን ተሰናበትኩት። አፍታ ሳንቆይ - ወዲያውኑ ከሸዋ ሲወጡ ለጎጃም የመጀመሪያዋ ከኾነችው የደጀን ከተማ ገባን። ከዓባይ ቆላ የእፎይታ ግልግል ይመስል፥ ደጀን አረፍ ብለን ቡና ብጤ ጠጣን።

ከደጀን ስንነሳ የገጠመን መንታ መንገድ ነበር። የብቸኛ መንገድ - በስተሰሜን ምሥራቅ ቀረ። ያመራነው በስተሰሜን ምዕራቡ - የቆላ ደጋ ዳሞት መንገድ ነበር። ጎዞ ወደ ደብረ ማርቆስ። ጢቅ፥ጎዳና ሚካኤል፥ሱማርጊ፥ጨሞጋ….. ገሰገስን። ኋላ ደብረማርቆስ ገባን። ምሳ ማርቆስ ኾነ።

በለጣቂው ጉዞም - አኹንም የቆላ ደጋ ዳሞት ከተሞችን ማቆራረጥ ነበረብን። ዓማኑኤል-ደምበጫ-ጂጋ- ፍኖተሰላም- ማንኩሳ- ቡሬ…… እያልን እንጅባራ ገባን። እንጅባራ ስንደርስ - ከፊሉን የጎጃም መንገድ አጋምሰን እንደነበር ተረዳኹ።

እዚኽ የጎጃም አካፋይ መንገድ - እንጅባራ ላይ ስንደርስ፥ ረጋ ብዬ እስካኹን ትኩረቴን የሳቡ ነገሮች ለማጤን ሞከርኩ። ሦስት የማይታለፉ ነገሮች አጋጠሙኝ። አንዱ፥ ከደምበጫ አንስቶ እዚኽ ድረስ፥ የተዘፈነለትን እውነተኛ የጎጃም ለምለምነት አረጋግጫለኹ። ኹለተኛው፥ በዚኹ ላይ ተዳምሮ - በተፈጥሮ ጥበቃ በኩል፥ የአዲስ- ባሕ የደን ዕፅዋት ማራኪ ልማት ነው። ሦስተኛው ግን - ቀድሞውንም የውሃ ነገር አይኾንልኝም - "እዚኽም አልለቀኝም!" ያሰኘኝም ነበር። ከእንጅባራ ታሪካዊነት ጋር የተያያዘ ነበር። አዎ! እንደቱሪስት ጀሮዬን ያቆመ ዜና እንጅባራ ላይ ሰማኹ። ከዋናው የመኪና መንገድ በስተምሥራቅ ትንሽ ገባ ብሎ፥ እንኳን ሀገሬው ስንቱ የፈረንጅ ዟሪ የባዘነበት አምባ መኖሩን ሰማኹ። አምባው ሰቀላ ነው። እና ታሪካዊ ምንጭ መኖሩን ተረዳኹ። ከዘመናት በፊት እነጀሮሜ ሎቦ፥ እነጀምስ ብሩስ፥ እነ ኤድዋርድ ሩፔል፥ እለሳሙኤል ጎባት፥ ወዘተ… የዓባይን ምንጭ ፍለጋ የማሰኑበት ሥፍራ ኖሯል!ታሪከኛ ምንጭ አለ! ምንጩም ግሼ መባሉን አወቅኹ ። የአገሬው "ቅዱሱ ወንዝ " (ጠበል?) መኾኑን ሰማኹ። ጥንት - ቅድመ ክርስትና አምልኮ ሥርዓት ሚፈጸምበት የቅዱስ ሚካኤልና የቅዱስ ዘርዓ ብሩክ ታቦታት እንደነበሩበትም አረጋገጥኩ። ያ "ቅዱሱ ምንጭ" አገሬው "ግልገል ዓባይ" የሚለው ጅረት ምንጭ ነው። ጀምስ ብሩስ ለዓለም ዝናውን የናኘለት የጥቁር ዓባይ መፍለቂያ ምንጭ - እዚኽ እንጅባራ አጠገብ ነበር የሚገኘው።

ከእንጅባራ - የቆላ ደጋ ዳሞትን ከተሞችን አቆራርጠን - ወደ አገው ምድር! የአገውን ከተሞች ቀሳንና ኮሶበርን አቆራርጠን ዳንግላ ገባን። ከዚያ ወደ ባሕር ዳር ከተሞች! የጎጃሞችን የስም አወጣጥ እያደነቅን - ከዳንግላ - ዱርቤቴ - መሸንቲ - መርዓዊ...እያልን ከምሽቱ 12 ሰዓት ተኩል ላይ ባሕር ዳር ገባን። እግዚኦ ጣና!!! የቢሾፍቱውን ሆራ - እንደውቅያኖስ ያዳንቅ የነበረ የትናንት ግምቴ ውሃ የፈሰሰበት፥ የካርታውን ሳይኾን የውኑን ጣና በዓይኔ በብረቱ ሳይ ነበር። አጀብ!!! ውሃ ውሃ ከሚያሰኝ አድካሚ ጉዞ በኋላ - አገር ከሚያኽል ውሃ- ምድር ከች!!! አይ ጎጃም ስም አወጣጥ!!! ከጣና ዳርቻ - እውነትም ባሕር ዳር!!!

የበረታ ድካምና ምሽቱ ተባብረው - ከጣና ዕይታ አቀቡን። የውሃ ባለሙያ፥ በዚኽ ላይ ከውሃ ምድር መጥቶ - እንደውሃ ወዳድነቴ - ጣናን ማየት አልቻልኩም። ይኹ ንና "እንዴት ይነጋል?" እያልኩ፥ ነገን ተስፋ በማድረግ ማረፊያ ፍለጋ ተሰማራን።

xxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxx

ነጋልኝ!! የጣናና የባሕር ዳር ነገርማ….!!! ከጣና ሀይቅ በስተደቡብ - በዘመናዊ እቅድ የተከተመችው ባሕር ዳር እውነትም ማራኪ ከተማ ናት። ምጥን ባለዘንባባ ከተማ!!!

እና ያን ዕለት ጧት - ድንግል ዓይኔን የማረኩት ኹለት ነገሮች አጋጠሙኝ። አንደኛው፥ ያለጥርጥር ያ የጣና ሀይቅ ነው። ይኹንና የነበረን የቆይታ ጊዜ ግማሽ ቀን ብቻ ነበርና ጣናን በጀልባ ሰንጥቆ ለመጎብኘት አልታደልኩም። ይኽም በመኾኑ፥ ለጣና የተመስጦ አድናቆቴን የገለጽኩት፥ በግዮንና በጣና ሆቴሎቻችን ሰገነት ላይ ተወስኜ ነበር።

ጉብኝቱ ቢቀርብኝም፥ ጣናን በዓይኔ ለማየት በመታደሌ ተጽናናኹ። ዕይታዬ ከስሚና ከንባብ ስንቁ ጋር አዋኅጄ - ጣናን ባሕር ዳር ዳርቻ ቆሜ - የልቤን ያኽል አወራኹት። እውነትም፥ ጣና በኢትዮጵያ ከሚገኙ ሀይቆች በስፋትም ኾነ በታሪካዊነቱ ተወዳዳሪ የለሽ ነው። ይኽ እንዲያ ተንጣሎ - ጎጃምንና ጎንደርን ኹለት የከፈለ ጉደኛ ሀይቅ፥ ከሰሜን ወደ ደቡብ 85 ኪሎ ሜትር፥ ከምዕራብ ደግሞ ወደ ምሥራቅ 65 ኪሎ ሜትር የተኛ ነው። ከውቅያኖስ ጠለል በላይም፥ 6ሺ ጫማ ገደማ ከፍታ ላይ መገኘቱም አስደንቆኛል።

ጣና - እንደሰንሰንሰለት በተያያዙና በአፍሪካም ታላላቅ በሚባሉት በ3ቱ እሳተገሞራዊ ተራሮች - ማለትም በአቡነ ዮሴፍ (13፣743 ጫማ)፥ በብርሃን (13፣625) እና በጉና (13፣881) ተራሮች መሀል - ሰማያማ የውሃ ግርማ ሞገሱን ተላብሶ - እውነትም በኩራት ተንጣሎ ይታያል። ይኼ "አገር የሚያኽል ውሃ!" ብዬ የሰየምኩት አብዬ ጣና 1500 ማይል ካሬ ስፋትና ወደ 1ሺህ ጫማ ጥልቀት እንዳለው ተረድቻለኹ።

ከመገረም በላይ፥ "ጣናን አያንስበትም!" ያሰኘኝ ሦስት ነገሮች ነበሩኝ። አንደኛ፥ ጣና እውነትም የኢትዮጵያ ወንዞች (ሀይቆች) አባት ነው። ምንጩ ግሼ ነው ቢባልም፥ ታላቁ ጥቁር ዓባይ ሾልኮ ይኹን መንጭቶ አገር የሚያካልለው - ከአንጋፋው ጣና ነው። ኹለተኛ፥ የውሃ እናት ወይም አባት ወደኾነው ወደዚኽ ግዙፍ ሀይቅ፥ 60 ገደማ የሚጠጉ ጅረቶች እንደሚገቡ መስማቴ ነበር። ሦስተኛ፥ በዚኽ ሀይቅ፥ በደን የተዋቡና በልዩ ልዩ የታሪክ ቅርሶች የዳበሩ ከ20 የሚበልጡ (40ም ይጠጋሉ ይላሉ) ጥንታዊና ታሪካዊ ደሴቶች መኖራቸው ነው። "እግዚኦ! ገዳም በገዳም

ደሴት!" አልኩ፡፡ "እዚኽ ውሃ አገር ላይ ስንቱን ደሴት አዳርሶ ማየት ይቻላል?" አልኩ፤... ብርጊዳ ማርያም፥ ማንድባ መድኃኔ ዓለም፥ ኀርኀራ፥ ዳጋ እስጢፋኖስ፥ ደቅ፥ ናርጋ ሥላሴ፥ ጣና ቂርቆስ፥ ምጽለ ፋሲለ ደስ፥ ክብራን ገብርኤል፥ ደብራ ማርያም፥ ዘጌ ወዘተ....እግዚኦ ደሴታት ዘጣና!!!

እንደኔ እንደኔ ጣና ደጃፍ ደርሶ ጣናን ተዟዙሮ ማየት ላልቻለ የኔ ቢጤ የቼዝማንን ዕድል ተመኘኹለት፡፡ ከታሪክ ንባቤ እንደተረዳኹት፥ የጣናን ውሃና ደሴት መሬቶቹን፥ በደሴቶቹም ላይ አፈር የቀመሱትን ነገሥታትና መናኒ ካህናቱን፥ እስከዛሬም የቆዩንን ቅርሶችና አስደናቂ እልፍ የሥነ ጥበባት ውጤቶችን፥ እንደ ክፍለ ዘመናችን ቱሪስት እንደ እንግሊዛዊው ቼዝማን ማንም አሳምሮና አብጠርጥሮ እንደማያውቅ ተረድቻለኹ፡፡ የቼዝማንን አጋጣሚ - አዎ- ዕድሉን እንደተመኘኹ - ከጣና ተለያየን!!

ኹለተኛው የባሕር ዳር ማራኪዬ ግን፥ ጢስ እሳት ዘዓባይ ነበር፡፡ ምናልባትም የጣና ቅሬታዬ የተካሰበትም ነበር፡፡ በቀረች የግማሽ ቀን ቆይታችን ከባሕር ዳር በስተደቡብ 30 ኪሎ ሜትር ገሰገስን፡፡ ተጉዘን ጫራ ጫራ ዳርቻ ደረስን፡፡ ልክ ከመኪና ስንወርድ፥ ፊት ሸዋንና ጎጃምን በሸለቆው ከፍሎ "ጉድ!" ያሰኘን አባይ፥ እዚኽ ደግሞ ጎንደርና ጎጃምን ከፍሎ -ቻ-ቻ-ቻ-ቻ-በሚል ገናን ድምጽ- አገር ሙሉ ሲስቅ ተሰማን!

ውሃ ሲስቅ እያሰብኩኝ ሳለ፥ ከሳቁ ዳርቻ ለመድረስ በእግር የግማሽ ሰዓት ጉዞ እንደሚቀረን ተነገረን፡፡ አይ የውሃ ኃይል!!! አይ ምትሀቱ!!! በምትሀቱ እየተሳብን፥ ያን ከእግር ጫማ የሚያወልቅ የጭቃ ጥርጊያ መንገድ ተያያዝን፡፡ እንዲያውም ይኼ ጥርጊያ መንገድ የቀናው፥ የእንግሊዟ ንግሥት ዳግማዊት ኤልሳቤጥ በ1958 ዐ .ም ኢትዮጵያን የጎበኘችና ጢስ ዓባይ የመጣች ጊዜ መኾኑን፥ ታሪኩን ሰማኹለት፡፡ አይደረስ የለ... ከዓባይ ሸለቆ - ሸለቆውን ለማቋረጥ ግን "የእግዜርን ድልድይ" ማቋረጥ ነበረብን፡፡ ተፈጥሮ ሰራሽ ሳይኾን፥ ሰው ሰራሹን - ድንቁን የፋሲል ድልድይ ግንብ! ልክ እዚኽ ጋ ጎጃምንና ጎንደርን እኩል በሚከፍለው ሸለቆ ላይ፥ በ17ኛው ክፍለ ዘመን አጼ ፋሲል ያሠሩት - ጥንታዊና ታሪካዊ ድልድይ ነበር፡፡ ልክ ስንሻገረው - ከጎጃም ጎንደር መሸጋገራችን ተነገረን - ያውም በደቂቃ ዕድሜ!

ከ5 ደቂቃ የእግር ጉዞ በኋላ - ጎንደር ምድር ላይ ኾነን፥ ከጫራ - ጫራ አቀበት ላይ ፥ ቁልቁል ሸለቆ እንደጉድ የሚምዘገዘገውን የዓባይን መዓተኛ ፏፏቴ ከነሕያዊ ግርማው ማየት የቻልነው፡፡ እስከዚያች ሰዓት ድረስ፥ ስደነቅ በኖርኩበት የፏፏቴው የፖስት ካርድ ምስል - ተውስታዬ አፈርኩ፡፡ ይኽን ማየት ብቻ እንጂ፥ መናገር ፈጽሞ አይገልጸውም፡፡ እግዚኦ የውሃ ኃይል! እግዚኦ የውሃ ውበት! ቢያዩት ፈጽሞ የማይጠግቡት! ደግሞ የፏፏቴው ውሃ ኃይልና ጉልበት - አስፈሪ ግርማው - ከድንቅ ተአምራዊነቱ በላይ፥ የሰውን ልጅ አቅም ኢምንት የሚያደርግ ነው፡፡ ባጠቃላይ "አጀብ! አጀብ !!" የሚያሰኝ ነው፡፡ ትርዒቱን ድንቅ የሚያደርገው - ፏፏቴው እየተምዘገዘገ ከሸለቆው የመጀመሪያ መግቢያው ላይ ሲያርፍ የሚረጨው ረጬት - ዓባይ ከሸለቆው አለት ሥር እየነደደ - በእውነትም የሚጤስ መምሰሉ ነው፡፡ ያ አካባቢውን የናኘ ትነት፥ በጠዋቲቱ የዐራት ሰዓት ፀሐይ - ልዩና ግርማዊ የኾነ፥ ታይቶ የማይጠገብ የቀስተ ደመና ውበት በአካባቢው ይፈጥራል፡፡ ይኼን "ጢስ-አባይ ፏፏቴ" ብቻ ተገኝቶ ማየት ነው-

ኃይሉን - ውበቱንና ምትሀታዊነቱን የሚያሳምን። በስተቀረ ይኸን ትዕይንት - በአሳን ሙርሄድ የአድናቆት መግለጫ ብቋጨው እመርጣለኹ። "...ጢስ ዓባይ - በመላው አፍሪካ - ዛምቤዚ ከሚገኘው የቪክቶሪያ ሕይቅ ብርቅ የፋፏቴ ውበት ለጥቆ፥ አቻ የማይገኝለት ድንቅ ትዕይንት ነው!!!..."

ከአድናቆቴ ጋብ ስል ነበር - ዓባይ ፋፏቴው ጎን - ለኃይል ምንጭነት ተጠልፎ - ለልማት መገበሩን የተረዳኹት። "ለካ የጫራ ጫራ የኤሌትሪክ ማመንጫ ኃይል ተቋም ያለው እዚኸ ኖሯል?" አልኩ። ጢስ ዓባይ ከቱሪዝም  መስህብነቱ ሌላ፥ ለልማት ሠልጥኖ ሳየው - የምኞቴ አንዳች ሙላት፥ መንፈሴን በሐሴት ናኘው። "ጢስ ዓባይ! -የዓባይ ውበት፥ የዓባይ ምትሀት - የዓባይ ኃይንና ልማት- አርአያህ ዘለዓለማዊ ነው!!" ብዬ ሌላ ቀን እንዲያገናኘን እየተመኘኹ - ከጢስ ዓባይም ተለያየን። ባሕር ዳርም መልስ አደረግን። ከምሳ በኋላ  ወደ ጎንደር ጉዞ ...ነበረብን።

"ባሕር ዳር ደኅና ቆዪን!" - ጉዞ ወደጎንደር!!! ገና ባሕር ዳር መውጫ ላይ ነበር አንድ ትዕይንት የገጠመን። ድልድይ!! ድልድይ መሻገር ነበረብን። የስዊዲሽ መሀንዲሶች እንደሠሩት ተረዳኹ። እንደ ጢስ ዓባዩ የፋሲል ድልድይ ኹሉ፥ ይኼም የጎጃምና የጎንደር መለያያ ድንበር ነበር። ይኸ ብቻ ሳይኾን፥ ዓባይ ከጣና ተለይቶ ሲወጣ በግላጭ ወለል ብሎ የሚታይበት አስደሳች አጋጣሚ ነበር። ድልድዩን ተሻግረን፥ አፍታውኑ ጎንደር ክልል ገባን።

ይኸ የከሰዓት በኋላ የጎንደር ጉዞኣችን - ከፊል ጎንደርን ያካተተ ነበር። እስከ ጎንደር ከተማ - ደቡብ ጎንደርን የሸፈነ ነበር። ባሕር ዳር፥ ሐሙሲት፥ ወሮታ፥ ዐዲስ ዘመን፥ ማክሰኚት፥እንፍራንዝ፥ ቆጋ፥ መሸንቲ፥ ጠዳ፥አዘዞን...አቆራርጠን አመሻሹ ላይ ጎንደር ከች ያልንበት ጉዞ ነበር።

ለኔ የዚኽ ጉዞ ውበት ኹለት ነበር። ጎንደር እስክንገባ ድረስ - ብዙውን ጊዜ ጣና ከዕይታችን ቢሰወርም- በስተ ምሥራቅ ከሥር ሥሩ ስንጓዝ ነበር የዋልነው። ከባሕር ዳር ጎንደር ድረስ - ጣናን ያኽል አገር እንደተጓዝን ተረዳኹ። ሌላው፥ ከዐዲስ ዘመን አንስቶ አዘዞ እስክንደርስ ድረስ - በሕይወቴ ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ሳያቋርጡ የተራራ ሰንሰለቶች የመውጣትና የመውረድ ድንቅ መልክአ ምድራዊ ትዕይንት ነበር - ያጋጠመኝ። ይኸን ኹሉ በስተምሥራቃችን ከሩቅ ኾኖ፥ የጉና ተራራ ሲታዘበን ለማምሸቱ እማኝ አለኝ።

በስተቀረ፥  ጓዳ ጎድጓውን ሳላየው ለቀረኹት የደቡብ ጎንደር - የቱሪስት ዋስ ዋቤ መጥራቱን እመርጣለኹ። ላገሩ እንግዳ ነኝና - የቱሪስትነቴ "ሞራሊቲ" ..ይኸን የሚፈቅድልኝ ይመስለኛል። እና የጀርመኑ ገናና ቱሪስት ኤድዋርድ ሩፔል (1794-18884) እጅጉኑ ትዝ አለኝ! እንዲያውም ግጥምጥሞሹም መልሶ እኔኑ ገረመኝ። ኤድዋርድ ሩፔል ጎንደር የመጣው - ምንም እንኳ ከእንግሊዞቹ ሳሙኤል ጎባት (1830)፥ ከክራፍ (1840)፥ ከኢዘንበርግ እና ጀምስ ብሩስ (1770) በኋላ ቢኾንም፥ እኛ ዛሬ የተጓዝነውን የደቡብ ጎንደር ምድር - ቀድሞውኑ እንደሱ አብጠርጥሮ የመረመረ ማንም አውሮፓዊ የለም።....

ሩፔል፥ ግብጽንና የዐረብ አገሮችን ተዘዋውሮ ያየ ዐዋቂ - ዐዋቂ ሰው ነበር፡፡ ታዲያ እኛ ውሎአችንን የተጓዝነውን ምድር መጓዙ ብቻ ሳይኾን እንዳስታውስ እንዳደነቀው ያደረገኝ - ከ150 ዓመታት በፊት አስቀድሞ፥ እኛ አኹን የምንጓዝበትን የፕሮጀክቶች ጥናት መሰል ዓላማ ቀድሞ ያከናወነ ጉደኛ አውሮፓዊ በመኾኑ ነው፡፡ ሩፔል፥ የሥነ ፈለክ ሊቅና የተፈጥሮ ሳይንስ ተመራማሪም ነበር፡፡ የደቡቡን ብቻ ሳይኾን ሰሜን ጎንደርንም ጭምር - የሰዉን ኑሮና ባሕል መሰለል ብቻ ሳይኾን፥ በየጋራ ሸንተረሩ እየተዘዋወረ የዕፅዋትና የዱር እንስሳትን ልቅም አድርጎ አጥንቷል፡፡ በዚኽ ላይ፥ የአካባቢ ጥናት ባለሙያነቱም ችላ የሚባል ያልነበረ ሲኾን፥ ብዙ የሜትሮሎጂ መረጃዎችንም ማጠናቀር የቻለ ጉደኛ ፈረንጅ ነበር፡፡

እንዲያው ያንዳንድ ሰዎች ውለታ ላለመጣል - እንግዲኽ ከሩፔል የኂላ ኂላ ነበር - የፈረንሣይ መንግሥት እ.ኤ.አ በ1840 ገደማ የላካቸው ፌፌትና ጋሊኒየር ከአድዋ እስከ ጎንደር ከተማ ድረስ - ከፍተኛ ግምት ሊሰጣቸው የሚችሉ የጂኦሎጂና የሜትሮሎጂ መረጃዎችን ለመጀመሪያ ጊዜ ያጠናቀሩት፡፡ በተመሳሳይ ኹኔታም፥ ከሩፔል በኂላ፥ እ.ኤ.አ ከ1839-1843 ጎንደር የቆየው ሌፌብሬ ምንም እንኳ የባሕር ኃይል መኮንን ቢኾንም፥ የጎንደር ዙሪያን የአርኪዊሎዢና የሥነ ሕዝብ ባሕል ልቅም አድርጎ ማጥናቱ ሊረሳ አይችልም፡፡ ይኼው እኛ ዛሬ….ከስንት ዓመታት በኂላ ገና በራሳችን ፍለጋና ምርምር እያልን ዳከራ ላይ አይደለን?!..

እና ለማንኛውም - ትንሽ ከፋሲሏ ጎንደር አረፍ እንበል፡፡ ነገ ሌላው ቀን….

*[ በለጣቂ..ማራኪ ነው ተብሎ የተነገረኝን የሰሜን ጎንደር---የተከዜን…. የአክሱም….የመቐለና የደሴ ዙሪያ ትዝብቶቼን ይዤ እስክቀርብ፥ በቸር ያገናኘን]*

xxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxx

# ጎንደር - አክሱም

አጀብ ጎንደር! ከአዲስ አበባ 743 ኪሎ ሜትር ርቀት! መቸም የውሃ ነገር አይኾንልኝም… በደቡብ ምዕራብ ታለቁ የደንዲር ወንዝ፥ በደቡብ ምሥራቅ ታላቁ የዓባይ ወንዝ፥ በሰሜን ምሥራቅ ደግሞ ታላቁ የተከዜ ወንዝ - ያዋስኗታል። አዎ! በእኒህ ሥሉስ አንጋፋ ጅረቶች እንብርት ምድር ላይ ያለችውን - የፋሲልን የሕልም ከተማ - ጎንደርን - በውን አየኋት። እንዳጋጣሚ ለሥራ የቆየነው ለኹለት ቀናት ነበር። እና ከሥራ በቀረው ሰዓት - ከፊል ጎንደር ጓዳ ጎድጎዳዋ አልቀረኝም ማለት እችላለኹ።

ግና ስንክሳር ስለሚወጣላት ጎንደር ምን ማለት እንደምችል አላውቅም። እንዲኹ በደፈናው ግን ጎንደርን ማየት ማለት እውነትም ከ17ኛው እስከ 19ነኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የኢትዮጵያ ዋና መዲና የነበረችውን ከተማ ማየት ማለት ነው። ወይንም ዛሬ ጎንደርን ማየት ማለት በእርግጥም ለ300 ዓመታት ያኽል ኖረው ያለፉባትን የ24 ነገሥታቷን አያና መታዘብና የመኻከለኛውን ዘመን ኢትዮጵያ የሃይማኖት፥ የጥበብና የባሕል ማዕከለ ምድር በገሀድ ምሥጢሩን መካፈል ማለት ነው።

መቸም ስለጎንደር - "አጀብ የጎንደር መንፈስ!" ብያለኹ። ያልኩትም - አስቀድሞ በቆረቆራት ጣውንታዊ መንፈስ መነሾ ነው። ጎንደርን የመሠረታት ፥ ዙሪያ አምባዋን ኹለት የከፈለ የደም አበላ ነውና ወይንም ጎንደር - የአባቱን ዕዳ ሊሸር ልጅ የመሠረታት የደም ካሣ ናት። አዎ!! ጎንደር - የሱስንዮስ ጸጸት፥ የፋሲለደስ ሐሴት !!!

ወይንስ የሞገደኛው ፔሮ ፓኤዝ እና የጉደኛው አልፎንዞ ማንዴዝ ጦስ ብንላት ይቀል ይኾን? ብቻ ታሪክ የነገረን ይኼን ነው።...... ጎንደር ሳትታለም በፊት፥ የዙሪያዋ አምባ ንጉሥ ሱስንዮስ (1599-1624) - ፊት ለቅድመ አያቱ የጦር ዕርዳታ መጥተው ኋላ ሀገረኛ ኾነው በቀሩቱ ጀዝዊት ሚሽነሪዎች ሃይማኖት ምርኮ ይኾናል። እና ፍጹሙ "ኮተሊኩ" ንጉሥ ከፓኤዝና ከአልፎንዞ ጋር ገጥሞ፥ ከነባሩ የ"ተዋኅዶ" ሀገረኛ - ከገዛ ሕዝቡ ጋር ደም ይቃባል። ኋላ እንደንስሐና ጸጸት - ከገነተ ኢየሱስ (አዘዞ አቅራቢያ) መንበሩ - ዙፋኑን ትቶ - ማዶ - ከጣናው ጎርጎራ ይሰደዳል። በዚኹ አያና ተነሳስቶ - ሕዝብ "ሃይማኖት ይመለስ፤ፋሲል ይንገስ!!!" ይላል። እና ዙሪያ አምባዋን ኹለት ከፍሎ ደም ላቃባ ጥፋት የደም ቁርሾና ካሣ ሥርየት ትኾን ዘንድ፥ ጎንደር ዛሬ አምባዋ ላይ - በአዲስ መንፈስ በ1624 ዐ.ም በፋሲለደስ ተቆረቆረች።…

ይኽ ጋራ አምባ ላይ የተቆረቆረችና ነዋሪዋም 80ሺህ ይገመት የነበረችው ጎንደር - ሕዝቧ ኹለት ዓይነት መልክ ነበረው። እና "የኩፋሌ(የመከፈል) ከተማ!" አልኩ። ምንም እንኳ ፋሲል ወዲያው እንደነገሠ፥ የፖርቹጋሎቹን ጀዝዊት ሚሽነሪዎች፥ በአዋጅ - ከአገሩ ሙልጭ አድርጎ

ቢያወጣቸውም፥ በወቅቱ አዲስ ፈላሲዎች ከሕንድ፥ ከአርመንና ከፋርስ መጥተውበት ነበር። እና ጎንደር ገና ከመቆርቆሯ ከተማዪቱ በመጤና በተወላጅ የተከፈለች ነበረች። ጎንደርን በኩፋሌ ባማት እውነቴን ነበር። ተወላጁ በከተማዋ እንብርት ሠፈረ፤ከተመ። ፋሲል መጤዎቹን - ከዐዲሱ ከተማው ራቅ ባለው ደቡባዊ ክፍል - ዐዲስ ዓለም ከተባለው መንደር እንዲሠፍሩ አደረገ። “አፓርታይድ በጎንደር!” አልኩ።

ላስታራቂ ያኽል ሦስተኞቹን ወገኖች ረሳኋቸው። ክልሶቹ ነበሩ። በግራኝ አህመድ ወረራ ጊዜ፥ ለልብነ ድንግል ርዳታ ከመጡቱ ኢየሱሳውያን ወታደሮች ካገሬው ሴቶች የተወለዱ ነበሩ። ጎንደር ስትቆረቆር 1,400 ገደማ ነበሩ። በእናቱ ተወላጅ የኾነ መጢቃ ትውልድ ነበርና እንደጎንደር ጌጥ....ከተወላጁ ጋር መኻል ጎንደር ከተመ። ከዚኽ ክልስ ትውልድ መኻል የተገኘችው ወለተ ጊዮርጊስ ናት - በኋላ የእውቁ የጎንደር ንጉሥ የበካፋ ሚስት እቴጌ ምንትዋብ - በቀጥታም ኾነ በተዘዋዋሪ ለ50 ዓመታት ያኽል ጎንደርን የገዛችው!

ያም ኾነ ይኽ - ገና ጎንደርን ስገጣጠማት፥ በስሜትም ኾነ በሐሳብ - አስቀድሞ ልረዳት የሞከርኩት የኹለት ተሟጋች መንፈሶች አውድማ ኾና ነው። በልብነድንግል - ገላውዴዎስና በአህመድ ግራ እጁ ዕጣ፥ እስልምናና ክርስትና ተፋልመውባታል። ኋላም እንደሱስንዮስ ጸጸት ካቶሊክና ተዋኅዶ ተፋጅቶባታል። በፋሲል ልማት እንኳ - መጤና ተወላጅ- አምባ ለአምባ ተራርቆ ከትሞባታል።

ይኼ ኩፋሌ መንፈሷ እንደተጠበቀ፥ ደግ ደጉን እናውራ ብንል እንኳ ጎንደር በልማቷም ለኔ የኹለት መንፈስ መገለጫ ናት። ሥጋዊና መንፈሳዊ - እጹብ ድንቅ ሕንፃ አብያተ ክርስቲያናትና ድንቅ የነገሥታት ግንቦች፥ ሃይማኖትና ኪነጥበብ፥ ንግድና ዕደጥበብ “ተዋኅዶ” ፈጥረውባታል።

ኋላ “ተዋኅዶ” እንዲፈጥርልኝ ልመኝ እንጂ፥ ጎንደር አድሬ እንደነቃኹ፥ ያው የለመደ ክፋይ መንፈሷ ሰፍኖብኝ ሳይኾን አይቀርም - የጠለፈኝ የ“ኩፋሌ” መንፈስ ነበር። እና ጎንደር አንዲት ኾና - እኔን አንዱን ሰው ኹለት ቦታ ከፈለችኝ።

ብቻ - ይኽን ምን ይሉት አላውቅም - አጀብ ጎንደር እንጂ!! ከደም ካሣ በቀር ምን ያልከፈልኩት አለ? የሚረዳልኝ፥ የኔን የጎንደር ጣጣ የቀመሰ ብቻ ነው። ባጭሩ፥ ጎንደር ውዬ ጎንደር ባድር “የሙያ ምች ” መታኝ። ነገር ሳላበዛ - በጎንደር የተነሳ፥ የፕሮፌሽንም መከፈል ገጠመኝ!!!

“ይኼ ያው የጎንደር መንፈስ መኾን አለበት! እንዲኽ ዓይነት መከፈል? ምን ነካኝ!?” ነበር ያልኩት። እስኪያስደነግጠኝ ድረስ - ስሜቴ በሃይድሮሊክስና በሲቪል ምሕንድስና ሙያ ተጻራሪ ስሜቶች መኻል ተከፈለ። እና የውሃ ምንድስና ባለሙያነቴ፥ የማይ አድናቂነቴ፥ የኢትዮጵያ መልክአ ምድራዊ የተፈጥሮ ውበትና ግርማ አፋዳሽነቴ፥ ...እዚያ ማዶ - ባሕር ዳርና ጣና ዳርቻ ተጎልቶ የቀረ ያኽል ተሰማኝ። እና ለዚኽ ያበቃችኝን ጎንደር እየታዘብኩ፥ በሠለጠነችበት የክህነት ቋንቋዋ “ መሀረኒ ሃይድሮሊክስ!” አልኩ። ባጭሩ፥ በጎንደር - የሃይድሮሊክስ ባለሙያነቴን ፈጽሞ ዘንግቼ “እኔ ሲቪል መሀንዲስ ብቻ ነኝማ” አልኩ።

ለነገሩ እኔም ኾንኩ ጎንደር ሀቅ ነበረን፡፡ አዎ! በሲቪል መሀንዲስነቴ ብቻ "ብኩራራም" ጎንደር ላይ ትክክል ነበርኩ፡፡ እዚኽም ኾነ እዚያ - ጎንደር በሃይማኖታዊውም ኾነ በዓለማዊ ኪነ ሕንፃዎቿ ፍጹም ምርኮ አድርጋኝ ነበርና ነው፡፡ እውነትም የፋሲል ጎንደር፥ ከልቧ - የ"ካስል" ከተማ ናት፡፡ ጎንደር ማለት - ባዳላኹለት ሙያዬ ዓይን - ጎንደር ምህንድስና ናት፡፡ ጎንደር አርክቴክቸር ናት!!! ለዚኽም - በከተማዋ ዙሪያና በራሷ በጎንደር እንብርት ላይ የሚገኙትና ከግራኝ፥ ከደርቡሽ፥ ከኢጣሊያና ከእንግሊዝ ጦር ጉዳት ተርፈው ዛሬ ለታሪክ ሕያው ኾነው የቀሩልን 15ቱ ያኽል የነገሥታቷ ካስሎች፥ ቪላዎች፥ ካናሎችና ድልድዮች፥ የ44ቱ አብያተ ክርስቲያናት ቅርሶቿ፥ ከኔ ተብታባ የአድናቆት ቃላት በላይ ብዙ ይናገራሉ፡፡ እና ኢትዮጵያውያን መሀንዲሶች "ኖራ አስነጥረው፥ ድንጋይ አስወቅረው…." በሠሯቸው እኒኽ ድንቅ ካስሎች ፊት፥ ያውም ጎንደር ከተማ ላይ "ሲቪል መሀንዲስ ብቻ ነኝ!" ባልል - ለራሴ ዋሽቻለኹ ነበር ፡፡ እና ጎንደርና እኔ አኹንም እንዲኹ በሙያ "ኩፋሌ" እንዲኽ ተኳኳንን፡፡

እና የምህንድስና ጥላ ጥላብኝ - ጎንደርን ያገኘኋት - የኢትዮጵያውያን ድንቅ የግንብ(ባታ) ርቀት፥ የኪነ ሕንፃ ውበትና የአርክቴክቸር ጥበብ መገለጫ ኾና ነበር፡፡ ይኽንንም ማንም ልብ ባይ በ70ሺ ካሬ ሜትር ላይ ተንጣሎ በአስደናቂ ቅጽር በታጠረው በባለ 12ቱ በር አንድ የፋሲል "ካስል" ግቢ ብቻ ታድሞ ያገኘዋል፡፡ ይኽ የጎንደር ድንቅ ሥፍራ - የፋሲልን ጨምሮ የ6 ተከታታይ ወራሲ ነገሥታቱ ጉደኛ "ሮያል ኮምፓውንድ" ነው፡፡ ታላቁን የፋሲል "ካስል"ን (1624-1659)፥ የጻድቁ ዮሐንስን(1659-1674)፥ የታላቁን ቀዳማዊ ኢያሱን (1674-1698)፥ የሣልሳዊ ዳዊትን (1710-1712)፥ የበካፋን (1714-1723)፥ የዳግማዊ ኢያሱን (1723-1747) እና የምንትዋብን ጉደኛ "ካስሎች" አየኹ!!! ገሚሱ ዛሬ ቢዘጋም፥ እግዞኦ… የቅጽሩ በሮች!!!….የነገሥታት ዋና በር፥ የአዛዥ በር የእምቢልታ በር፥ የቋሊ (ሙሽራ) በር፥ አደናግር በር፥ የተዝካር በር፥ የወንበር በር፥ የዣን ተክል በር፥ የልዕልታት በርና የርግብ በር!! እኔ ኹለት ተከፍዬ ቀረኹ እንጂ - ጎንደርስ መውጫዋ ዐሥራ ኹለት!!!..

እንዲያው በምህንድስና ዓይን - እኒኽ ኹሉ ቢተነተኑ በወደድኹ ነበር፡፡ ጊዜውም፥ ቦታውም አይፈቅድልኝም፡፡ ይኹንም ቢባል እንዲኹ በድፍረት በኹለት ቀን መላ ብቻ የሚወጡትም አይመስለኝም፡፡ እንጂ..ባለ32 ሜትር ከፍታው ታላቁ የፋሲል "ካስል"፥ የታላቁ ቀዳማዊ ኢያሱ ለየት ያለ "ካስል"፥ የሣልሳዊ ዳዊት የሲምፎኒ አዳራሽ፥ ባለ 9ኙ በሮች የበካፋ "ካስል"፥ የምንትዋብ "ካስሎች"፥ ….ስንት የሚነገርላቸው ነበሩ፡፡ ከዚኽ "ኮምፓውንድ" ውጪ፥ በጎንደር አቅራቢያ ባሉት አምባዎች ያሉትን የደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን፥ የፋሲል መታጠቢያ፥ የምንትዋብ የቁስቋም ቤተክርስቲያንና ቤተ መንግሥት፥ ልደታ ማርያም፥ ቅዱስ ዮሐንስ፥ የሚካኤል ስዑል ቤተ መንግሥት ስንቱ ተቆጥሮ ያልቃል?!

"አኹንም ያው የጎንደር መንፈስ ነው!" ያሰኘኝ ሌላ ነገርም ገጠመኝ፡፡ ካስሎቹን በምህንድስና ዓይን መተንተኑን አልዳፈር ብል እንኳ፥ ከማይለቀኝ ጥያቄ ጋር ተቆራኘኹ፡፡ እሱም፥ ያው ኹለት ቦታ አሳምሮ ከፈለኝ! "አኹን እኒኽን ድንቅ ካስሎች የሠሩት እውነት ኢትዮጵያውያን መሀንዲሶች ወይስ መጤዎቹ?" የሚል ነበር፡፡

ወይ ፍርጃ!!!... ከአድናቆቴ የተነሳ፥ የዚያን ዘመን ሥልጡን ኢትዮጵያውያን መሀንዲሶችን በዓይነ ኅሊናዬ ማየት አቃተኝ። እና በመጀመሪያ፥ ኢትዮጵያውያን መሀንዲሶች ሊሠሩት አይችሉም ብዬ በ"ፍርደ ገምድል"ነት ፈረድኩባቸው። ፈረድኩ ከማለት ተጠራጠርኳቸው ማለት ሳይቀል አይቀርም። ይኽን ያስባለኝ፥ ያ የጢስ ዓባዩን - የመጀመሪያ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ድልድይ - ዋቢ በማድረግ ነው። ፊት ጢስ ዓባይ ዳርቻ ቆሜ ፋሲል እንዳሠራው የተናገርኩትን ያንን ድንቅ ድልድይ ያሠራው ሱስንዮስ ነበር። እና የጢስ ዓባዩን ድልድይ በምህንድስና ኃላፊነት ያስገነባው፥ ከእስፓኙ ኢየሱሳዊ ከአልፎንዞ መንዴዝ ጋር በ1617 ከሕንድ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ሕንዳዊው መሀንዲስ አብዱል ከሪም የሚባል ግለሰብ መኾኑን ጎንደር ከገባኹ በኋላ አረጋግጫለኹ። ይኽ ብቻ ሳይኾን፥ ሱስንዮስ በድንጋይ፥ በኖራና በእንጨት - በአዘዞ፥ በሊቦና በጎርጎራ ከተሞቹ ያሠራቸው ቤተ መንግሥቶቹ ያሠራቸው ቤተ ክርስቲያኖች በእኒያው ኢየሱሳውያን በተባሉ ካቶሊካውያን ሚሲዮናውያን፥ በግብጽና በሕንድ የቴክኒክ ባለሙያዎች መኾኑ የተረጋገጠ ነው አሉኝ። ለጊዜው ስሙን አላገኘኹትም እንጂ የሕንፃ መሀንዲሱ አንድ ኢየሱሳዊ (አብዱል ከሪም እራሱ?) እንደነበር ማስረገጫ ሳይኾን ይቀራል?

ኋላ ደግሞ..."የለም ኢትዮጵያውያን ናቸው እንጂ!" ብያለኹ። የኢየሱሳውያን ነገር ከተነሳ፥ ፋሲል በ1925 ዐ.ም ካገር ሙልጭ አድርጎ አስወጥቷችል። የቀረም ቢኖር፥ በሕይወቱ ፈርዷል። እና "የውጭ መሀንዲስ የሚባል ነገር አልነበረም። የፋሲልንና የተቀሩትን ነገሥታት አብያተ መንግሥታት (ካስልስ) የሠሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው። እንኳን በፋሲል ጊዜ፥ በሱስንዮስ ጊዜ ኢትዮጵያውያን መሀንዲሶች ነበሩን! " አልኩ። ለዚኽ ማስተማመኛ የኾነኝ፥ ሱስንዮስ ዘጠኝ ዓመታት ፈጅቶ (1612-1621) በደንቀዝ ያሠራውን ቤተ መንግሥቱን በምህንድስና ኃላፊነት ያሠራው ገብረክርስቶስ የሚባል ኢትዮጵያዊ እንደኾነ ማረጋገጫ አለ። ታዲያ በ"ሮያል ኮምፓውንዱ" ውስጥ የሚገኘው ያ ትልቁ የፋሲል ካስል፥ በቅርጽ ካልኾነ በቀር፥ በአሠራር ጥበብ አኳያ ከሱስንዮስ የደንቀዝ ቤተ መንግሥት በምንም አይለይም። የፋሲልን "ካስል" አንድ ሕንዳዊ መሀንዲስ ሠራ የሚባል ጭምጭምታ ብሰማም፥ የሌሎቹም ተከታታይ ካስሎች ጣጣም አለና...ኢትዮጵያውያን መሀንዲሶች ለመሥራታቸው መጠራጠር አላስፈለገኝም። ኢትዮጵያዊ አሻራቸው ብቻ ይበቃኛል። "የኮርቻ ግንብ"፥"የቀጭን ፈታይ ግንብ"፥"የዝንጀሮ ራስ"፥...የተሰኙቱ አጠራሮችና ውቅር "ስታይላቸው" የኢትዮጵያውያን መሀንዲሶች ለመኾኑ የሚያጠራጥር ነገር የለም።

ጎንደር ከተማን - ከኹለት ቀናት ቆይታ በኋላ የተለየኋት በዚኽ መሰሉ ትዝታ ነበር። ለጣቂው ጉዞ ወደ አክሱም የ350 ኪሎ ሜትር ጉዞ ነበር።

xxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxxx

**ወደ አክሱም….**

የዕለቱ የጠዋቱ ጉዞ፥ ሰሜን ጎንደርን የማቆራረጥ ነበር፡፡ በመጀመሪያ የተጓዝነው የወገራን አውራጃ ነበር፡፡ ዋልዋጅ፥ ኩስጌ፥ አምባ ጊዮርጊስ፥ ገደብጌ፥….እያልን ከዝነኛዪቱ ዳባት ከተማ ገባን፡፡ ገና 35 ኪሎ ሜትር ነበር የተጓዝነው፡፡ ግን ቀስ በቀስ ወደ ከፍታ አምባ እየወጣን መኾኑን እየታዘብኩ ነበር፡፡ እና ዳባትን አየኋት፡፡ በወያኔ-ደርግ ጦርነት ወቅት በኹለቱም ወገኖች መኻል "በመያዝና በመለቀቅ ሪከርድ የያዘች ከተማ!!!" አልኩ፡፡

ከ13 ኪሎ ሜትር ጉዞ በኋላ፥ የወገራን አውራጃ ጨርሰን፥ ወቅን ገባን፡፡ የለጠቅነው የሰሜን አውራጃን ነበር፡፡ ብዙም ሳንቆይ፥ ከደባርቅ ከተማ ገባን፡፡ "ስሜን ሆቴል" ቁርስ አደረግን፡፡ ለካ ደባርቅ፥ ወደ ስሜን ተራሮች የሚኼደው መንገድ መነሻ ከተማ ናት፡፡ 3020 ሜትር ከፍታ ከውሃ ጠለል በላይ መገኘቷንም ሰማኹ፡፡ የስሜን ተራሮች ከደባርቅ ወደ 40 ኪሎ ሜትር ገደማ ላይ እንደሚርቁ ተነገረኝ፡፡ ግን ከዚኽች ከተማ ላይ ተኹና በግላጭ አይታዩም ነበር፡፡

ከቁርስ በኋላ፥ ቁርጥ ያለ - ውሃ ውሃ የሚያሰኘውን ጉዞ ጀመርን፡፡ ሌላ ተአምር ያጋጠመኝ - ከደባርቅ አንድ 15 ኪሎ ሜትሮች ከኼድን በኋላ ነበር፡፡ "ላንድ ስኬፕ" እንዲያ በውበት አስደንግጦኝ አያውቅም፡፡ ከወደ ሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ - በርቀት - እንደጉድ የተጠላለፉ ሰማይ ጠቀስ የጋራዎች ትዕይንታዊ ሰልፍ አየኹ!!! በዚኹ ተመስጦ እያለኹ - ጥቂትም ሳንቆይ ከአንድ ሽለቋማ ጫፍ ደረስን፡፡ ባልዘነጋ የወልቃፊት ሰርጥ ሳይኾን አይቀርም፡፡ ለካ ከጉዱ ሊማሊሞ ጫፍ ላይ ነበርን!!

ዘይገርም! አዎ! ከጉዱ ሊማሊሞ ሽለቆ ጫፍ መንገድ ጀመርን፡፡ ከአፋፉ ስንገባ - አፋፉ ያለበት የምድር ከፍታ የጽርሐ አርያምን ከፍታ ያኽል ሲኾን፥ መዳረሻ ታቹ ፈጽሞ ፍጻሜ የማይገኝለት የሚመስል - ምድረ ፋይድ- ጭልጥ ያለ - እንጦርጦስ ነበር፡፡ ይኽንንም መንገድ የጀመርነው - ምንም ከወደ ግራ በኩል ተገን በሌለው ጭው ያለ ገደል፥ በተራራው ጥግ ጥግ እንደጉድ ተሰርስሮ በተሠራ የሠርጥ መንገድ ላይ ነበር፡፡ ያንን ቁልቁል እንጦርጦስ መውረድ የጣር ያኽል ነበር፡፡ ከማሳቀቁ የተነሳ ዓይን የሚያስጨፍን ነበር!!! ዓይኔን ጨፍኜ ሞከርኩት፡፡ ምኑን አምኜ እጨፍናለኹ?!?…..ወይ ጉዱ ሊማሊሞ!!! አሃ!!! የጸጋዬ ገብረመድኅን "ሊማሊሞ"!!!…ቅኔው በዚያ ቅጽበት እንደማጽናኛ ያኽል ያዋዛኝ ገባ፡፡ ትዝ አለኝ!!!…..

…………………………………………………..

እንደፍካሬ ኢየሱስ ቃል፥እንደሙታን የግዞት ሕግ

ተውተብትቦ፥ ተጥለፍልፎ፥ ተቆላልፎ እንደዛር ድግ

በምድር በሰማይ ዳር ድንበር በህዋው ዓለም ክልል ጥግ

በሲያል ጠፍር መሰላል የብስ ከጠፈር ታድሞ

ጥጉን እንደራዕዩ አውታር፥ ከነአክናፉ ቁልቁል ዘሞ

እንደእንጦርጦስ በር አጥር፥ በአለት ናዳ ተረምርሞ

የጉም ክንዱን እንደጦር፥ ወደምድር ማጎጸን ቆልምሞ

እንደባቢሎን ግንብ አጥር፥ ቋንቋ ለቋንቋ አሳድሞ

አልበገር አልደፈር አልሰበር ያለን ከርሞ

ሊማ - ሊሞ የቁም እርሙ፥ ጠፈር አዘል ሊማ - ሊሞ

ሰማይ ከምድር ተደላድሎ፥ ተኮትኩቶ ተከርክሞ

በደማሚት ተፈልፍሎ፥ ድልድይ ይሁን ሊማ-ሊሞ?!

……………………………………………………

ያን ቁልቁል የእንጦርጦስ ጉዞት፥ እጅግ በሚያስደንቀውና በጣሙን በሚያሳቅቀው የጋራ ጥግ ጠመዝማዛ መንገድ ተያያዝነው፡፡ ከአምስት ደቂቃ ጉዞ በኋላ፥ እዚያ ሚያሰቅቅ ሠርጥ መንገድ ላይ፥ አንዲት የጋራ ሥር ምንጭ አገኘን፡፡ ከመኪና ወረድን፡፡ መታጠፊያ ሠርጥ ላይ ነበረች፡፡ ልክ እንደጠበል  በእጅ እፍኛችን - እየቀዳን ተጎነጨን፡፡ በዚያ የበረሀ ንዳዳም ሸለቆ ላይ የበረሀ ገነት ምንጭ ማለት ነበር፡፡ ቅዱሱ ውሃ ከመጣፈጡ በላይ ቅዝቃዜው!!!? ለአካል የሚሰጠው እርካታ! ይኼ ኹሉ ለተወሰነ ደቂቃ ያኽል፥ የሊማሊሞን አስፈሪነት ወደ አስደሳች መስክነት የሚለውጥ - አጭበርባሪያችን የነበረ ትዕይንት ነበር፡፡….

ከምንጭዋ እርካታችን ሌላ፥ የሊማሊሞ ጠመዝማዛ መንገዶች - ቁልቁል እንደዘንዶ በተረተሩ ሰርጥ ላይ ተጠምጥመው አዘቅት የሚወርዱበትን ትዕይንት ያየነው - እዚያው መታጠፊያው ጠርዝ ላይ ካለች አንዲት ጉደኛ ቦታ ላይ ነበር፡፡ እግዞኦ ሊማሊሞ!!! ቦታዋ ታሪካዊ በመኾኗም እውነትም ለትዝብት የቆመች (የተሠራች) የተፈጥሮና የሰው ሰገነት ናት፡፡ “ለመኾኑ ይኽን አስደናቂ የአለት ጋራ በምን ጥበብ፥ በምን ዘዴ፥ በምን መሥዋዕትነት፥ በምን ያኽል ጊዜ፥ እነማን ሠሩት?!” በሚል አሰላሳይ አጠይቆት ላይ ነበርኩ፡፡ “እግዚኦ የሊማሊሞ ኢንጅነሪንግ!!! እዚያ ጎንደር- የአርክቴክቸር ጥበብ! እዚኽ ደግሞ የመንገድ ኢንጂነሪንግ - ጎንደር ምኗ ነሽ?” አልኩ፡፡ ምናልባት ከምጽዋ - አሥመራ መኻል ( ዛሬ አገር ከአገር ተለይቶ..) አለ ሚባለውን ተደናቂ መንገድ ባላየውም፥ በኢትዮጵያ ውስጥ የሊማሊሞን ያኽል አስደናቂ መንገድ ፈጽሞ ያለ አይመስለኝም፡፡ ይኽን ሰሜን ኢትዮጵያን ከምዕራብ ኢትዮጵያ የሚያገናኝ አስደናቂ የሸለቆ ሠርጥ መንገድ፥ ነፍስን ሸጦ - አለት ፈልፍሎ፥ ቋጥኝ ንዶና ደልድሎ እንዲኽ የተደላደለ መንገድ መሥራት መቻም ተአምር ነው!!!

“ማን ሠራው? ሲቪል መሀንዲሱ ማነው? ማነው?” ነበር - ጉጉቴ፡፡ ያቺ ታሪካዊ ሰገነት አፍታ ሳልቆይ ምላሽ ሰጠችኝ፡፡ ያን ድንቅ መንገድ መሥዋዕት ከፍለው ለሠሩ ኹሉ፥ የመታሰቢያ ሐውልት ኖራለች!!! በኢጣሊያ የኢትዮጵያ ወረራ ወቅት (1928-1933 ዐ.ም) - የኢጣሊያ መንግሥት ያቆመው ሐውልት ነበር፡፡ ጽሑፉ በጣሊያንኛ!!! “አሃ! ጣሊያን መሀንዲሶችና ኢትዮጵያውያን የቀን ሙያተኞች!!!” የሚል ሐሳብ መጣብኝ፡፡

ወዲያው ያረጋገጥኩት፥ በአምስቱ ዓመት የኢጣሊያ ወረራ ወቅት መሠራቱን ነበር። ስለሊማሊሞ መንገድ የኢንጅነሪንግ ጥበብና ግንባታ ሌላ፥ የሚገርመው - ይኽ ድንቅ የሸለቆ አዘቅትና ሠርጥ መንገድ - በምን የወረራ ፋታ ሊሠራ እንደቻለ ነው። ጣሊያን- የአገር አርበኛ በየቦታው ፋታ እየነሳው እንደምን ተረጋግቶ ሠራው? የገረመኝ ይኼ ነበር። ወይንም አንድ ጊዜ አንድ አዛውንት ያሉኝ - ስላቅ እውነት ይኾን ወይ? አልኩኝ።.....

"ዱቼ ሙሶሎኒ ራሰ መላጣ

መንገድ ሊሠራ እንጂ መች ሊገዛ መጣ?!"

ይኽን እያሰላሰልኩ፥ የአዘቅት ጠመዝማዛ ጉዞኣችንን በዐዲስ ጉልበት ጀመርን። ጥያቄዬ አልተመለሰም ነበርና - ከታሪክ ንባቤ አንዳንድ ነገሮችን በጥሞና ማሰለሳሰል ያዝኩ። ለአፍታም ያኽል ...የጸጋዬ ገብረመድኅን "ሊማ-ሊሞ" ጣልቃ ገባ.....

..........................................

ከጠፈር ውሃ ገድቦ፥ ለየብስ እንደማገር ቆሞ

ተጠማዞ ተጠምጥሞ

ከጽንፍ ጽንፍ አረምሞ

ከደባርቅ እስከ አዲአርቃይ

አለት ከደመና በላይ

አዘንብሎ እንደሰማይ

እንደጠፈር ሽቅብ ሲታይ

ጉም አጥልቶ እንደቀሚሱ

ጸሐይን እንዳንገት ልብሱ

ተከናንቦ ተሸላልሞ

ተንደላቆ ሊማሊሞ

......................................

ሊማ - ሊሞ ጉዱ የተሠራው፥ በእውቁ የኢጣሊያ የመንገድ ኢንጂነሪንግ ጥበብ፥ በኢጣሊያውያን ነበር። ጥያቄው "በጦርነት ወረራ ሰዓት፥ በፍልሚያ ውስጥ ምን ጊዜ አግኝተው ነው?" የሚለው ነው። ከላይ ያልኩት የሽማግሌው ምጸታዊ ግጥም አንዳች ፍንጭ ቢኖረውም፥ ከታሪክ የምንረዳው የበለጠ ማረጋገጫ አለው። ኢጣሊያ ለወረራው በቂ ዝግጅት ማድረጓን ታሪኳ ይመሰክራል። ከወረራው ጎን ለጎን - የልማት መሠረተ አውታሮችን መዘርጋት ዋነኛ እቅዷ

ነበር፡፡ ከልማት መሠረተ አውታሮችም ዋነኛው የመንገድ ሥራ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ እና ይኽን ሰሜን ኢትዮጵያን ከምዕራብ ኢትዮጵያ የሚያገናኝ ዓይነተኛ የተራራ ሰንሰለትና ረባዳ ሸለቆ ሰንጥቃ መደልደል ነበረባት፡፡

"እናስ?" የሚያሰኝ ነው፡፡ እና አኹን ጉዞ በጀመርንበት በጎንደር - አክሱም መሥመር ላይ፥ ቋሚ ጦሯ በነበረው በአንደኛው ክፍለ ጦሯ ውስጥ ብቻ፥ 10ሺህ ካሚዮኖችና ሞተር ብስክሌቶች፥ 70ሺህ የጭነት አጋሰሶች እና 90ሺህ የሀገር ተወላጅ የመንገድ ሠራተኞች የነበሩበት ብርጌድ ነበር፡፡ ኋላ እንደተረዳኹትም ተወላጁ ኢትዮጵዊ - ገሚሱ በግዞት መልክ፥ ገሚሱ በዕለት ቀለብ፥ ገሚሱ በወር ራሽን ተይዞ፥ በዚያ አስፈሪና አደገኛ የሸለቆ ሠርጥ ላይ እየተንጠለጠሉ በመከራ ሠርተውታል፡፡ እናም መሀንዲሶቹና ኦፕሬተሮቹ ጣሊያኖች ይኹኑ እንጂ - ብዙ ኢትዮጵያውያን ቋጥኝ እየተደረመሰባቸው፥ አለት እየፈነከተ እየቆረጣቸው፥ ገደል እየገቡ እየሞቱ በመሥዋዕትነት ሰርተውታል፡፡ እና ሊማ - ሊሞ የኢጣሊያውያን ሕልም፥ የኢትዮጵያውያን ድንቅ መሥዋዕትነት ያስገኘው፥ አስገራሚ የመንገድ ኢንጂነሪንግ ጥበብ የሚታይበት ጉደኛ መንገድ ነው፡፡

እና ገጣሚና ባለቅኔ ብኾን፥ ከጸጋዬ ቅኔ ፍላት በላቀ ስለ ሊማ - ሊሞ እቀኝ ነበር፡፡ ዱዳ ልቤ ግን የተፈጠመው.....በዚያው በጸጋዬ የሊማ - ሊሞ ትዝብት ብቻ ኾኖ ቀረ፡፡

……………………………………..

የሰማይ የምድሩ ኬላ፥ የየብስ የጠፈሩ ዋልታ

አይበገር የአለት ጣራ፥ አይመክተው መከታ

ሊማ - ሊሞ አድማስ ሰበሩ፥ በጎማ ፈለግ ይረታ?

በትሬንታ እግር ይረታ?

……………………………………..

ዛሬ እንደስለት ሃጅ ፈለግ፥ በግብረ ጉንዳን ተተልሞ

ሰማይ ከምድር ተደላድሎ፥ተኮትኩቶ፥ ተከርክሞ

በድማሚት ተፈልፍሎ፥ ድልድይ ይሁን ሊማ - ሊሞ?

…………………………………………

ይልቅ "ነገርን ነገር ያነሳዋል"...በሊማሊሞ አያያዝ፥ ያኔ ኢጣሊያ በመንገድ ሥራው ላይ ስለነበራት አቋም ኋላ ጊዜ የሥራ ሚኒስትሯ የነበሩት ኮቦሊጃሊ ገለጡት እንደሚባለው - በኢትዮጵያ ውስጥ ሊሠሩት አቅደውት የነበረው - 9936 ኪሎ ሜትር ርዝማኔ የነበረው የባቡርና የመኪና መንገድ ነበር፡፡ ከዚያ እቅዳቸው ውስጥ 6995 ኪሎ ሜትር የሠሩ ሲኾን፥ 3342 ቱ ኪሎ ሜትር የአስፋልት መንገድ ነበር፡፡ "አጀብ!" አልኩኝ፡፡ ለዚኽም ያወጡት ወጪ ከ80 እስከ 100 ሚሊዮን ፓውንድ የሚገመት መኾኑን ተረድቻለኹ፡፡

ለዚኹም ስገረም፥ የ“ደንከል”(አፋር) - አሰብ መንገድ ትዝ አለኝ፡፡ እኚያው የኢጣሊያ የሥራ ሚኒስትር ገለጹት እንደሚባለው የደንከሉ(የአፋሩ) መንገድ ብቻ 175 ሚሊዮን ሊሬ ፈጅቷል፡፡ ጠቅላላ መንገዱ 7 ሚሊዮን 460 ሺህ ስኩየር ሜትር ሲኾን፥ 34ሺህ ስኩየር ሜትሩ በአስፋልት የተሠራ ነው፡፡ በዚኽ የመንገድ ሥራ መሥመር ላይ፥ አራት ታላላቅ ድልድዮችና 1504 አነስተኛ ፉካዎችና ድልድዮች አሉ፡፡ መንገዱን ለማጠናቀቅ 17 ሚሊዮን የሥራ ቀናት የፈጀ ሲኾን፥ መንገዱንም ለመሥራት 32ሺህ ኢትዮጵያውያን ተካፋይ ኾነዋል፡፡ “እንግዲኽ በዚኽ ዓይን - የጎንደር - ሊማሊሞ - ተከዜ - አክሱም መንገድ ምን ያኽል ሠራተኞች፥ ምን ያኽል ወጪ፥ ምን ያኽል የሥራ ቀናት ፈጅቶ ይኾን?” አልኩ፡፡ አወይ ሊማሊሞ ጉዱ!!!.....

ጎንደርም ኾነ ሊማ-ሊሞ- ፈጽሞውኑ የሲቪል ምህንድስና ሙያዬን እንዳፋድስ ስላደረጉኝ - የሕንጻ ኢንጂነሪግና የመንገድ ኢንጂነሪንግ አቦካቶ ብኾን አትቀየሙኝ፡፡ እና ያን ጉደኛ የሊማሊሞ መንገድ አዘቅቱን መውረድ የጀመርነው - እኔ በዚኽ ተመስጦኦ ውስጥ ሳለኹ ነበር፡፡ አዎ! “መቸም ጣሊያን ያኔ ባይሠራውና ባያሠራው ኖሮ እስከ ምጽአተ ዓለም ድረስ ፈጽሞ አንገነኛኝ ይኾን ይኾን??”.... እያልኩ ሽለቆውን ቁልቁል እየተጠማዘዝን ወረድን፡፡ ከአኹን አኹን “ገደል ገባን!” እያልን በስጋት ከድብ ባሕር ገባን፡፡ ሰርጡ ላይ በተገኘች አንዲት ረባዳ ሥፍራ ላይ ቲንጥ መንደር!! ለሷ ስገረም፥ ጥቂት ኼደን ዛሬማ ምትባል የሠርጥ ላይ መንደር!! ኋላም ጥቂት ተጉዘን ጨው ባሕር! ትንሽ ፈቅ ብለን የተከዜ ወንዝ ገባር ነው የተባለ የአምባር ወንዝ! የአውራ ጎዳና ሠራተኞች ሊማ-ሊሞን ሲጠግኑ አየን፡፡ ከቅርቡ የእርስ በርስ ጦርነት በኋላ መኾኑ ነው፡፡ “እባካችኹ ጥንቃቄውን ካላወቃችኹበት ሊማ - ሊሞን አትንኩት!” አልኩኝ በልቤ፡፡ እና በዚኽ ኹናቴ ነበር - ከእንጦርጦሱ የመጨረሻ አዘቅት ከአዲ አርቃይ የደረስነው፡፡ የመጣነው ከወልቀፊት ጫፍ እዚኽ ስምጥ ድረስ 40 ኪሎ ሜትር ነበር!

ለካ የመጣነው- የወረድነውን ያኽል - የአቀበት መልስ ጉዞ ነበረብን!!! ወይ ሊማሊሞ! ከአንዱ የተራራ ሰንሰለት ወደ ሌላኛው፥ ከአዘቅት ወደ አቀበት ሽቅብ መውጣት - እንዴት ማራኪ ጉዞ ነበር?! ከዚኽ የአቀበት ጉዞኣችን መኻል ላይ ስንደርስ አንድ አስደናቂና ማራኪ ትዕይንት ገጠመን፡፡ “የአፍሪካ ሰማይ ጠቀስ ጣሪያዎች” - የተሰኙቱ የስሜን ተራሮች - ከርቀትም ቢኾን ወለል ብለው ታዩን!! ያ 40 ኪሎ ሜትር ይርቃል የሚባለውን ርቀት - እቅርባችን የኾኑ ያኽል ከነማራኪ ግርማቸው በደስታ ስሜት አየናቸው፡፡ ብዙም ሳንቆይ - በተጠማዛዡ የሊማሊሞ መንገድ አስገዳጅነት - ወዲያው ተሰወሩብን፡፡ ብዙም ሳንዘገይ ብር ማርያም ከተባለቸው የሠርጥ መንደር ላይ ደረስን፡፡ በ50 ሜትሮች ርቀት ላይም ኹለት መለስተኛ ጅረቶች አገኘን፡፡ እንደሰማኹት የታላቁ የተከዜ ወንዝ ገባሮች ናቸው፡፡ ትንሿ ጉያ መባሏን አረጋገጥኹ፡፡ እነዚኽ ወንዞች፥ ከፊል በረሀማ ለኾነው ሊማሊሞ - እንዴት ያለ የበረሀ ገነትነት እንደሰጡት በቀላሉ የውሃ ፋላቸው ይመሰክራል፡፡ እና ከተራራ ሰንሰለት፥ ተራራ ሰንሰለት እየተጠማዘዝን፥ ከከፍታ ከፍታ እየወጣን - ከአንድ ጉደኛ አምባ ወጣን፡፡ ሊማ- ሊሞን የጨረሰ ማር ይገባዋል!!!! እና ማይ ጸምሪ ነበር የገባነው፡፡ እንደተረዳኹት፥ ከአዲ አርቃይ የሊማ - ሊሞ አዘቅት እስከ ማይ ጸምሪ አምባ ድረስ 63 ኪሎ ሜትሮች ነበር የመጣነው፡፡ ወይ ጉድ ሊማ - ሊሞ!!! ማይ ጸምሪ ለምሳ ወረድን፡፡ ምሳ በላን፡፡ ማር በላን!!! ማይ ጸምሪ በአኹኑ ዐዲሱ አከላለል የትግራይና

የጎንደር አዋሳኝ ድንበር ከተማ መኾኗንም ተረዳኹ፡፡ እና የሊማ - ሊሞን ውጣ ውረድ ማይ ጸምሪ ላይ ለአፍታ ያኽል እፎይ አልን!!!

ከዚያ የሊማሊሞ ጉድ ወጥተን፥ ሦስት ኪሎ ሜትር ያኽል ሜዳ ሜዳውን ቆረጥነው፡፡ ልክ እዚኽ አካባቢ ነበር - በአፍሪካ ካሉት 10 ታላላቅ ተራሮችና በኢትዮጵያ ታላቁ የራስ ዳሸን የሚገኝበትን የሰሜን ተራሮችን - እንደገና በአስደናቂ ግርማቸው ያየናቸው፡፡ በዚኽ የአድናቆት ተመስጦ፥ ከአባ ማጽሬ ደረስን፡፡ ጎንደርን ጨርሰን ትግራይ ገብተን ኖሯል!! ለካ የነበርነው - ከታላቁ የተከዜ በረሀ ሸለቆ አፋፍ ላይ ነበረ!!!

አጀብ ተከዜ!!! በስሚ ብቻ - ጆሮ ጠገቡ ከኾንኩት ከዝነኛው ተከዜ ወንዝ መግቢያ ደረስን፡፡ ለነገሩ ገና የሊማ - ሊሞ ብዥታ አልወጣልኝም ነበር፡፡ ይኹንና በዚያኑ ቅጽበት፥ ሊማ - ሊሞ የቅርብ ትዝታ ኾኖ፥ ተከዜን አበርትቶ አናፈቀኝ፡፡ አዎ! የተከዜ እንግዳ ኾንኩ!!

አወይ ተከዜዋ ኾይ!!! "አንተስ ምን ዓይነታው አገር ትኾን?" አልኩ በልቤ፡፡ የዓባይን ሸለቆ - ጉድ አገር ስል ነበር፡፡ እሱን የሚያስንቅ - ሊማ-ሊሞን የመሰለ ጉዳጉድ ገጠመኝ፡፡ በሊማ - ሊሞ ዓይን የዓባይ ሸለቆ መለስተኛ ጉድባ ነበር የኾነብኝ፡፡ "ተከዜ ደግሞ የምን ትዝብት ያመጣብኝ ይኾን?" አልኩ፡፡ እና ተከዜን ገና ሳላየው - ተከዜን የማየት ብርቱ ጉጉት - ገና ከሸለቆው ዳርቻ ናጠኝ!!......

እና የተከዜን ሸለቆ ቁልቁለት - አዘቅት መውረድ የጀመርነው በዚኽ የጉጉት መንፈስ ነበር፡፡ ተከዜ በረሀ - እኛ እንግዶቹን - በሀሩር ንዳዱ ተቀበለን፡፡ ይኹንና ያን ጉደኛና ሰንሰለታማ የሸለቆ ጎርጅ ማዘቅዘቅ ጀመርን፡፡ "አወይ ተከዜ!" አልኩት፡፡ ከሸለቆው ስምጥ ለመድረስ ቢያንስ ቢያንስ ግማሽ ሰዓት በላይ እንደሚፈጅብን ተረዳኹኝ፡፡ እና ይኽን ቁርጤን ሳውቅ ነበር - በውል የለየኊቸው ሦስት አራት ሐሳቦች ያመሱኝ፡፡.....

መጀመሪያ ጫን ጫን ያስተነፈሰኝ - የጂኦግራፊ ተማሪነቴ ትውስታ ነበር፡፡ ውስጤ ገኖ የነበረው - የጎንደሩና የሊማሊሞው የሲቪል ምህንድስና ተአብዮዑ እዚኽ ከተከዜ በረሀ - በጂኦግራፊ፥ በስታትስቲክስና በሃይድሮሊክስ ሙያዎች ተመስጥኦ ውስጥ ገባ፡፡ እና ከኹሉም ቀድሞ፥ የዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዓመት የጂኦግራፊ ኮርሴ ትውስታ ገዛኝ፡፡ ያ ከኊላ ያደነቅኹት ሊማ- ሊሞና ገና ወደፊቴ ምዘልቀው ተከዜ አንድግ ኾነው በኢትዮጵያ መልክአ ምድራዊ ገጽታ - ካርታ ላይ ያላቸውን ሥፍራ ማስታወስ ያዝኩ፡፡

እምዬ- ጂኦግራፊ ዘኢትዮጵያ !!!.....ያገሪቱ መልክአ ምድር - ቆላ፥ ወይና ደጋና ደጋ ተብሎ በሦስት ይከፈላል፡፡ ከባሕር ጠለል በታች ያለው ኹላ ቆላ ይባላል፡፡ ከባሕር ጠለል እስከ 1ሺህ ሜትር ከፍታ ድረስ ደግሞ ወይና ደጋ፡፡ ከ1ሺህ እስከ 2ሺህ ሜትር ከፍታ መለስተኛ ደጋ ሲባል፥ ከዚያ በላይ ግን ከፍተኛ ደጋማ ሥፍራ ይባላል፡፡ ኢትዮጵያውያን የጂኦግራፊ ሊቃውንት እንደሚሉት፥ ከኢትዮጵያ ጠቅላላ 1,250,282 ካሬ ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት ውስጥ 769,000 ካሬ ኪሎ ሜትሩ ወይም 61 በመቶው ቆላማ መሬት ነው፡፡ የቀረው 482,282 ካሬ ኪሎ ሜትሩ ደጋማ (ደጋና ወይና ደጋ) መሬት ነው፡፡ ይኸም ከሀገሪቱ ጠቅላላ መሬት 39 በመቶ መኾኑ

ነው፡፡ 50 ሚሊዮን ከሚገመተው ሕዝባችን መኻል፥ 93 በመቶው ያኽል የሚኖረው በደጋማው የሀገሪቱ ክፍል ነው የሚልም መደምደሚያ አላቸው፡፡

በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ - የኢትዮጵያ ምድር የአፍሪካ የውሃ ምንጭና ጋን ነው መባሉን - ተከዜ በረሀ ላይ ማሰብ ያስቸግራል፡፡ ይኹንና ታላቁ የምሥራቅ አፍሪካ የስምጥ ሸለቆ፥ የኢትዮጵያን ምድር በሰሜን ምዕራብና በደቡብ ምሥራቅ የተራራ ሰንሰለቶች ይከፍላል፡፡ “”እኔና ተከዜ እንግዲኽ በሰሜን ምዕራብ ነው ያለነው!” አልኩ፡፡ የአገሪቱ ከፍተኛ ሥፍራ የሚገኘው እኔና ተከዜ ባለንበት በሰሜን ምዕራብ፥ በራስ ደጀን (ራስ ዳሸን?!) ተራራ ላይ ሲኾን የእሱም ከፍታ ከባሕር ጠለል ወደላይ 4543 ሜትር ነው፡፡ “ዝቅተኛውስ?” አልኩ፡፡ ዝቅተኛው ሥፍራ ደግሞ በሰሜን ምሥራቅ በቀይ ባሕር አጠገብ የዳሎል ስምጥ ሸለቆ ቦታ ሲኾን፥ የእሱም ዝቅታ ልክ ከባሕር ጠለል ወደ ታች 116 ሜትር ነው፡፡ “ግን የተከዜ በረሀ ከባሕር ጠለል በታች ምን ያኽል ይሸልቅ ይኾን?” የሚልም ጥያቄ ተደቀነብኝ፡፡

ይኽን የሚመልስልኝ - ተከዜ ያለበት ደጋማው - የሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ጂኦግራፊያዊ ኹኔታ እንደኾነ ተረዳኹ፡፡ ይኹንና ኢትዮጵያውያን ጂኦግራፊስቶች የኢትዮጵያን ደጋማ ከፍተኛ ሥፍራዎች በሦስት ይከፍሏቸዋል፡፡ እነሱም አንደኛ፥ የኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ደጋማ ሥፍራዎች (ከሀገሪቱ ምድር 17.98 በመቶ)፥ የኢትዮጵያ ምዕራባዊ ደጋማ ቦታዎች (44.69 በመቶ) እና የደቡብ ምዕራብ ደጋማ ቦታዎች 33.33 በመቶ ናቸው፡፡

“እንግዲኽ አቦይ ተከዜ የሚገኘው በምዕራብ ኢትዮጵያ ደጋማ ሥፍራ ውስጥ ነው - ያለው!” አልኩ፡፡ አኹንም ኢትዮጵያውያን ጂኦግራፊስቶች የምዕራቡን ደጋማ ክፍል በ5 አቀጣጫዎች ይከፍሉታልና “የተከዜስ ኹነኛ ሥፍራስ?” አልኩኝ መልሼ፡፡ አንድ የኤርትራ - ትግራይ ከፍተኛ ደጋማ ሥፍራ፥ ኹለተኛ- የአንበሳ ባርካ የሰሜን ማዕከላዊ ደጋ፥ የሸዋ ከፍተኛ ደጋ አምባ፥ የደቡብ ምዕራብና የደቡብ ምሥራቅ ደጋማ ሥፍራዎች ናቸው፡፡

ሊማ-ሊሞም ኾነ ተከዜ የሚገኙት - በመጀመሪያዎቹ ኹለቱ ከፍተኛ ደጋማ ሥፍራዎች ውስጥ አማካይ ቦታ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከፊሉ ተከዜ በኤርትራ - ትግራይ ከፍተኛ ደጋ ውስጥ ኾኖ፥ ከደቡብ ኤርትራው የሐማሴን ተራሮች ምዕራብ ምዕራቡን ይዞ፥ ወደ ደቡብ አኹን እስካለንበት ተከዜ ሸለቆና አልፎም ወደ ምዕራብ እስከ ጸለምትና ወልቃይት ብሎም ሱዳን ጠረፍ ድረስ ይዘልቃል፡፡ ገሚሱ የተከዜ ተፋሰስ ደግሞ በጎንደር፥ በጎጃምና በውሎ መኻል ባሉት የዓባይና የተከዜ ተፋሰስ መካፈያ (ላስታ-ሰቆጣ አምባ) በኾኑት የሰሜን ማዕከላዊ ከፍተኛ ደጋማ ሥፍራዎች ውስጥ ይገኛል፡፡

እንግዲኽ ተከዜ በከፍተኞቹ ደጋማ ሥፍራዎች ይኹን እንጂ፥ የተከዜ በረሀ - ያላንዳች ጥርጥር ቆላማ ነው፡፡ ተከዜ ደጋማም ቆላማም ነው፡፡ “አምባ ላይ ቆላ?!” ብዬም ተገረምኹ፡፡ አኹንም የቆላማነቱን ጠባይ ለማማት፥ የጂኦግራፊ ትምህርቴን ትውስታ ተማጠንኩኝ፡፡ አዎ! ለማስታወስ ሞከርኩ፡፡ ተከዜ ባገሪቱ ከፍተኛ ደጋማ ሥፍራዎች ውስጥ ካሉ ቆላማ ሥፍራዎች አንዱ ነው፡፡ እነሱም አምስት ናቸው፡፡ የአንሰባ ባርካ ቆላማ ሸለቆ፥ የተከዜና የሰቲት ቆላማ ሥፍራዎች፥የዓባይና የዲንዲር ቆላ እና የጊቤ ቆላ ናቸው፡፡ አዎ! ተከዜ ሚገኘው፥ በተከዜና በሰቲት ቆላማ መደብ ውስጥ ነው!!!

የኾነ ነገር ትዝ አለኝ!! ባገሬው ቋንቋ “ተከዘ” ወይም “ተከዜ” ማለት - ጅረት ወይም ፋል ወይንም ወንዝ ማለት ነው ማለትን ሰምቻለኹና። እና የተከዜ ወንዝ ፥ በክልሉ ካሉት ከፍተኛ ደጋማ ቦታዎች መኻል፥ ወደ 3ሺህ ጫማ ያኽል አዘቅት ሸለቆ የሚፈስ ነው። ከባሕር ጠለል ግን ምን ያኽል ሜትር እንደሚወርድ አላወቅኹም። ይኹንና የኛ የውሃ ባለሙያዎች የኢትዮጵያን የውሃ ተፋሰሶች በ4 ሲከፍሏቸው፥ ኢትዮጵያውያን ጂኦግራፊስቶች ግን በ3 እንደሚከፍሏቸው የትምህርት ቤት ትዝታዬ አስታወሰኝ። አንደኛ፥ የስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች (አዋሽና የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች)፥ የደቡብ ምሥራቅ ተፋሰሶች(ገናሌና ሸበሌ) እና ተከዜ ከነአጋሮቹ የሚገኝበት የምዕራብ ኢትዮጵያ ተፋሰስ ናቸው።

እንደገና የምዕራብ ኢትዮጵያን ተፋሰሶች ለማስታወስ ሞከርኩ። እነሱም ኹለት ዓይነት ናቸው። የመጀመሪያው፥ የሰሜን ምዕራብ ተፋሰስ ነው። አንሰባ፥ ባርካ፥ ተከዜ፥ አንገረብ፥ ጉአንግ፥ ዓባይ እና ባሮ ሲኾኑ - ከኢትዮጵያ ወጥተው ወደ ምዕራብ በመኼድ በሱዳን ከነጭ ዓባይ ጋር የሚቀላቀሉ ናቸው። ኹለተኞቹ፥ የደቡብ ምዕራቦቹ የኦሞና የጊቤ ወንዞች ናቸው። ወደ ምዕራብ በመፍሰስ ከሩዶልፍ ሐይቅ ጋር ይቀላቀላሉ።

ወደ ተከዜ ባተኩር ይሻላል። ተከዜ አምባም ቆላም ነው ብለናል። የተከዜ ወንዝ - በምሥራቅ ከደንከል ተፋሰስ፥ በሰሜን ከአንገረብ - ጋሽ ተፋሰስ፥ በደቡብ ከዓባይ ተፋሰስ፥ በምዕራብ ከሱዳን ይዋሰናል። የተከዜ ምሥራቁ ደጋማ ሲኾን፥ ምዕራቡ ደግሞ ቆላማ ነው። ደጋውንና ቆላውን ጨምሮ ተከዜ በ22,600 ስኩየር ኪሎ ሜትር ላይ የተንጣለለ ነው። በቆላማው ክፍሉ 3,000 ጫማ ወደታች ሸለቋማ የኾነው ተከዜ፥ በደጋማው ክፍሉ ደግሞ ከ3,000 ጫማ ከፍታ በላይ ያላቸው የሀገሪቱ ከፍተኛ ተራሮች የሚገኙበት አምባ ነው። ራስ ደጀን (ዳሽን 4,620 ሜትር)፥ አምባ አቢየር (3,793 ሜትር)፥ ሃይ አምባ (4፣175 ሜትር) እና አቡነ ዮሴፍ (4፣190 ሜትር)…….

ይኼኔ- ከውሃ ባለሙያነቴ አንጻር - ተከዜን አጥብቄ ማሰላሰል ያዝኩ። ማለትም የጉዞኣችን አካል በኾነው - በውሃ ሀብት ልማት አግጣጫ። ተከዜን - በውሃ ኃይል፥ በመስኖ ልማትና በትራንስፖርት ልማት አቅጣጫ አብሰለሰልኩት። ግን እግዚኦ የተከዜ በረሀ ንዳድ…..!!!

ከእሳተ ገሞራ ፈሳሽ በቅዝቃዜ የተፈጠረ ጥልቅና ለም የአፈር ሀብት ያላት ሀገራችን፥ እንደ ተከዜ ካሉ ከሰሜንና ከምዕራብ ተራራዎች በሚፈልቁ የኢትዮጵያ ታላላቅ ወንዞችዋ “የምሥራቅ አፍሪቃ አምባና የውሃ ጋን!” ተብላ ትጠራለች። በእርግጥም ኢትዮጵያ፥ በተፈጥሮ ከፍተኛ የኾነ የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር የውሃ ሀብት ያላት አገር ናት። “እንደተከዜ ያሉ ዘማች ወንዞቻችንን በምን ዓይነት ነው እዚኹ ጠልፈን ለልማት ማዋል የምንችለው?” የኔ ብቻ ሳይኾን፥ የማንኛውም ቅን ኢትዮጵያዊ ጥያቄ ነውና ተከዜን ከስሜት ይልቅ፥ በውሃ ባለሙያዎቻችን የቅርብ ጥናት ዓይን የተደረሰበትን ቅኝት ለማጤን ሞከርኩ።

ኤርትራ ድንበር ውስጥ በከፊል ካለው ክልሉ ጨምሮ፥ የተከዜ ተፋሰስ በጠቅላላው 90ሺሕ ስኩየር ኪሎ ሜትር ይኾናል። ከጠቅላላው የሀገሪቱ ተፋሰሶች፥ ተከዜ 7.8 በመቶውን ይሸፍናል። ይኽም ከሀገሪቱ ጠቅላላ ሕዝብም 7.9 በመቶውን የሚያቅፍ ነው። አማካይ፥ ዓመታዊ የውሃ መጠኑም 7.63 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ሲኾን፥ ከዚኽም ውስጥ ጥቅም ላይ

(ለውሃ ኃይልና ለመስኖ) ሊውል ይችላል ተብሎ የተገመተው 5.73 ቢሊዮን ሜትር ኩቡ ነው፡፡ ይኸም ከጠቅላላው የሀገሪቱ የውሃ ሀብት 5.9 በመቶ ነው፡፡

በሀገሪቱ ከፍተኛ ተፋሰሶች አንጻር- ተከዜ - ከዓባይ (ከጠቅላላው ተፋሰስ 17.5 በመቶ) ፥ ከዋቢ ሸበሌ (ከጠቅላላው ተፋሰስ 17.4 በመቶ)፥ ከገናሌ (ከጠቅላላው ተፋሰስ 14.9 በመቶ)፥ ከአዋሽ(ከጠቅላላው ተፋሰስ 9.8 በመቶ) ቀጥሎ በ5ኛ ደረጃ (ከጠቅላላው ተፋሰስ 7.8 በመቶ) የሚገኝ ነው፡፡ በኤሌትሪክ ምንጭ ኃይልነቱም - ከዓባይ (በሰዓት 798635 ሚሊዮን ኪሎዋት በሰዓት)፥ ከዋቢ ሸበሌ (21563.3)፥ ከመረብ - ጋሽ (17450)፥ ከኦሞ (16067) ቀጥሎ ተከዜ በሰዓት 14846.5 ሚሊዮን ኪሎዋት ሊያመርት እንደሚችል ይገመታል፡፡ ይኹንና ከዚኽ ውስጥ ትክክለኛ ሥራ ላይ ሊውል ይችላል ተብሎ የተገመተው 5047 ሚሊዮን ኪሎዋት በሰዓት ነው፡፡

ከዚኽ በተጨማሪ፥ የተከዜ ተፋሰስ ከመቶ 50 እጁ ለእርሻ የሚኾን ተስማሚ አፈር ያለው በመኾኑ፥ ለመስኖ ልማት የሚጋብዝ ኾኖ ተገኝቷል፡፡ ምንም እንኳ በድርቅና በጦርነት ምክንያት የአካባበቢው ተፈጥሮ ጥበቃ በመጓደሉ - ያለው ለም አፈር ከዕጽዋት በመራቆቱ፥ በውሃና በነፋስ መሸርሸርና መታጠብ ቢያጋጥመውም፥ ከተፋሰሱ 60 በመቶ እጅ አኹንም ዝናብ የሚያገኝ ነው፡፡ የተፋሰሱን ክልል 600 ስኩየር ኪሎሜትር ያኽል የሰሜን ከፍተኛ ተራሮች ቢይዙትም፥ የተቀረው ክፍል ሊለማ የሚችል ነው፡፡ የቅርብ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት፥ ከተፋሰሱ 11.9 በመቶ ቁጥቋጦኣማ፥ 21.7 በመቶ ደግሞ ጠፍና የግጦሽ መሬት ሲኾን፥ ደናማ ሥፍራው 7 ከመቶ ብቻ ነው፡፡ የተቀረው ለእርሻ ሊውል የሚችል ነው፡፡ 312,700 ሄክታር መሬት በመስኖ ሊለማ እንደሚችል ተስፋ ተደርጓል፡፡

በውሃ ትራንስፖርት በኩል፥ በኢትዮጵያ ውስጥ ከባሮ ወንዝ በስተቀር ምቹነት የሌለው በመኾኑ፥ በዚኽ በኩል የተከዜም ወንዝ አስተዋጽኦ ባዶ ነው ይባል ይኾን?! ይልቅ በምድር ትራንስፖርት በኩል፥ በተከዜ ተፋሰስ ዙሪያ የ2,253 ኪሎ ሜትር የመኪና መንገድ አለ፡፡ ከዚኽ ውስጥ የበጋ መንገድ ብቻ 1,431 ኪሎ ሜትር ሲኾን፥ የበጋና ክረምት መንገድ 822 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን አለ፡፡ ከመሠረተ ልማት አንጻር እኒኽ የ2,253 ኪሎ ሜትር መንገዶች፥ ነዋሪያቸው ከ2ሺህ በላይ የኾነ ሕዝብ የሚኖርባቸው 29 የተፋሰሱን ዙሪያ ከተሞች ያገናኛሉ፡፡ ከነዚኽ ከተሞች የመቐለ ከተማ 61ሺህ ነዋሪዎች ገደማ ሲኖሯት፥ ከተፋሰሱ ዙሪያ ከተሞችም ትልቋ ናት፡፡

ከዚኽ በስተቀረ፥ ተከዜ ደጋማው፥ ተከዜ በረሀው - የወርቅ፥ የብረት፥ የማንጋኒዝ፥ የእብነ በረድ፥ የመዳብና የዚንክ ማዕድናት ሀብቶች እንዳሉት አንዳንድ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ተፋሰሱ በልውጤ አለቶች የተገነባ ሲኾን፥ ከሜሶዞኢክና ከሴኖዞኢክ የአለት ምሥረታ ጂኦሎጂአዊ ዘመናት የተገኙቱ የሲሚንቶ፥ የኖራና የአስቤቶስ ሀብቱ ለመሠረተ ልማት ግንባታና ለእንዱስትሪ እንዲኹም ለማዕድን ልማት ተስፋ ያለው ነው፡፡

ይኽ የልማት ተስፋ ከሚያመጣው ተጨባጭ ውጤት በስተቀር፥ የተከዜን በረሀና ሸለቆ ንዳድ ያየ እንዲኹ ጉድ ይላል፡፡ እና ከግማሽ ሰዓት የነፍስ ግቢና የነፍስ ውጪ የቁልቁለትና የአዘቅት ጉዞ በኋላ....አ!!!...ከትልቁ የተከዜ ወንዝ ደረስን፡፡ በኹለት ግዙፍ ድልድዮች ታጅቧል፡፡ ስንደርስ በስተግራ በኩል ያለው በእርስ በርሱ ጦርነት ሰዓት የፈረሰ ነው፡፡ ገሚሱ ጎኑ ከወንዙ

ተጋድሟል፡፡ በጤነኛው ድልድይ ላይ፥ በአድናቆት ስሜት ተከዜን ከሥር እያየን ተሻገርን፡፡ ተሻግረን ከታላቁ የተከዜ ወንዝ ጋር ከመኪና ወርደን ተያየን!!!

መጀመሪያ፥ በዚያ ታላቅና ሰፊ ወንዝ ላይ የተሠራውን ድልድይ አየኹት፡፡ ከዓባይ ድልድይ ትንሽ ረዘም የሚል ሲኾን፥ ከወንዙ በላይ ግን ከፍታው ከ30 ሜትሮች ያኽል በላይ አይርቅም፡፡ ድልድዩ የተሠራው፥ ከዓባይ ሸለቆ መለስተኛ በኾነ፥ በአንጻሩ ሜዳማ ቦታ ላይ ነው አልኩ፡፡ በዚኽ ዓይን “ሰላማዊውና ምቹው ተከዜ!” ብዬ አደነቅኹኝ፡፡ በአድናቆት ብቻ አልተመለስንም፥ እወንዙ ፋል ድረስ ወረድን፡፡ ለማስታወሻ ያኽልም፥ የአካባቢውን - የወንዙን ልዩ ልዩ ኅብረ ቀለማዊ የአለት ድንጋይ ዓይነቶች ሰብሰብን ወጣን፡፡ አወይ ተከዜ!!!

ተከዜ ከልቡ በረሀ ነው!!!....የተከዜን አቀበት መልሶ የመውጣት አድካሚ ጉዞ ነበረብን፡፡ ”አዘቅቱን የመውረድ ያኽል ይፈጅብን ይኾን?” እያልኩ ነበር፡፡ የበረሀው ንዳድ - በሀሩር የገረሩትን ዛፎች አልፎ አልፎ ሲያጤስ ይታይል፡፡ በረሀው ከቁጥቋጦ በስተቀር፥ የዕጽዋት ደኑ የተመናመነ ነበር፡፡ በገላጣው ላይ እንደ ተአምር ነፍስ ዘርተው የሚታዩቱ የዕጣን ዛፎች መኾናቸውን ተረዳኹ፡፡ የተከዜ ተፋሰስ በዕጣን ዛፍ ሀብታም መኾኑንና ይኽም ለውጭ ንግድ ከፍተኛ ገቢ የሚያስገኝ መኾኑን በቀላሉ  መገመት አያስቸግርም፡፡ “ምነዋ ተከዜ ታዲያ?!” አልኩ፡፡

የተከዜን ሸለቆ አቀበት እየወጣን - የማስተር ፕላን ጥናትና የልማቱን ተጨባጭ ውጤት እያሰላሰልኩ ነበር፡፡ “ይኽ እንግዲኽ በሕዝቡ ዓይነተኛ ፍላጎት፥ በክልሉ ኃላፊዎችና በባለሙያዎች ጥረት ሊከናወን የሚችል ነው፡፡“ አልኩኝ፡፡ እስከዚያው ድረስ.....

እስከዚያው ድረስ ....አቀበቱን እየወጣን ስለተከዜ “ይኼ የዓመጸኞች ዋሻ!” የሚል ሐሳብና ትዝብት መጣብኝ፡፡ አዎ! ከቅርቡ - በጸረ ደርግ አቋም የተሰለፈ ተፋላሚ ኹሉ መሸጎ የተደራጀበት አምባ ነውና - በተጋዳዮቹ ዓይን በትዝታ አየኹት፡፡ ሌላው፥ በኢጣሊያ - ኢትዮጵያ የ5ቱ ዓመትም ወረራ ጊዜ፥ ተከዜ የኢትዮጵያን አርበኞች የነጻነት ምሽግ በመኾን አገልግሏል፡፡ የካቲት 23 እና 26/1928 ዐ.ም  ከፍተኛ ተጋድሎ ተፈጽሞበታል፡፡ ተከዜና አርበኞቹ በመጨረሻ የተረቱት ጨርሶ ባልጠበቁት የኢጣሊያን የመርዝ አይሮፕላኖች ነበር፡፡ ኢጣሊያኖች፥ በራስ እምሩ ይመራ በነበረው ጦር ላይ፥ 25,000 ያኽል የሚኾን የመትረየስ ጥይትና ውሃውን ከሚበክል መርዝ ላይ አጸዱንና ሰውን በሚፈጅ የመርዝ ጢስና እሳት አርከፍክፈውበታል፡፡ 63 የኢጣሊያ መኮንኖችና 894 ያኽል የኢጣሊያን ወታደሮች ቢያልቁም፥ ከኢትዮጵያ ጦር የተረፈው 300 ሰው ገደማ ብቻ ነበር፡፡ እና  ያኔ የተከዜ በረሀ ከዳር እስከ ዳር በእሳት ተንቀለቀለ!!! ተከዜ በዚኽ መልክ ከተማረከ በኋላ ነበር - ሊማ-ሊሞ ተሰብሮ ጎንደር የተያዘቸው!!! ቢኾንም “ ተከዜ! የወንዶቹ አገር አምባ!!!” አልኩ፡፡

ተከዜ በረሀ ኾኖ ምን ማይታሰብ አለ? የኛኑ መሰል ተጓዦች - ማለት የጥናት ቃኚ ቡድን ከኋላ ታሪክ መፈልፈል ያዝኩኝ፡፡ ጠመዝማዛውን የሸለቆ አቀበት እየወጣን ነበር፡፡ እና ተከዜን በመቃኘት፥ እንግሊዞችን የሚወዳደር የለም፡፡ ለዚኽ በ1762 ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረው ስኮቲሹ ጀምስ ብሩስና ጣሊያናው ረዳቱ ሉጂ ባሉጋኒን አያሌ መረጃዎች ከላይ ስለአክሱም፥ ከታች ስለጎንደርና ጣና፥ ከመሀል ደግሞ ስለሰሜን ተራሮችና ከሰሜን ተራሮች ሥር

ስለሚመነጨው የተከዜ ተፋሰስና ዙሪያ ባጠቃላይ 25 ቅጽ ሙሉ ሐተታ የዘገቡ ናቸው፡፡ እና እነጀምስ ብሩስ - የተከዜን በረሀ የዛሬ 200 ዓመት ቃኝተውታል፡፡ "ሰልለውታል" ማለት ይቀል ይኾን? "ምን ምን ብለው ይኾን?" አልኩ፡፡

ከብሩስም በኋላ ቢኾን፥ በተለይ ተከዜን በወግ የሰለሉ እንግሊዞቹ ናቸው፡፡ ዋና መዲናቸውን አንጣሎ ላይ ከነበረው፥ ከወቅቱ የትግራይ ገዥ ከራስ ወልደ ሥላሴ ጋር ጥብቅ ግኑኝነት የመሠረተውና በቀይ ባሕር ላይ የሃይድሮግራፊክ ሥራ ይሠራ የነበረው ቪስካውንት ቫሌንቲያ - ባልደረባውን የባሕር ኃይል መኮንን ሄንሪ ሳልትን (1772-1820) ከሦስት እንግሊዛውያን የካርታ ባለሙያዎች ጋር ይልካል፡፡ ራሱ በሥነ ሥርዓት ተቀብለው ያስተናግዷቸዋል፡፡ አክሱምን፥ አድዋን፥ ተከዜን ዙሪያ በሄንሪ ሳልት መሪነት ብጥር አድርገው ለመሰልል ችለዋል፡፡ በተለይ በተከዜ ዙሪያ ያደረጉት አጥጋቢ ጥናት፥ ኋላ ስለክልሉ ጂኦግራፊያዊ ኹኔታና ማኅበራዊ - ኤኮኖሚያዊ ጥናትና መረጃ፥ እንደመልካም መነሻና እንዲያውም የማያዳግም እንደኾነ ይነገራል፡፡ ሄንሪ ሳልት "Voyage to Abyssinia" በሚል እ.ኤ.አ በ1814 በለንደን ያሳተመው የጉዞ ዘገባው፥ ስለተከዜ ተወዳዳሪ የሌለው ታሪካዊ መረጃ ነው፡፡

ቀጥሎ ፈረንሣዮችን የሚያኽል የለም፡፡ በ1822 ገደማ የመጡት ቀዳሚዎቹ የተከዜ ቃኝዎች ኮምበስና ታሚሲየር ባይቀናቸውም፥ የኋለኛውን አንቶኒዮ ዲአባዲን (1802-1890) የሚያኽል የለም፡፡ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ከወንድሙ ከአርናውድ ጋር በ1840 ገደማ ነበር፡፡ የጣናን ጥልቀት መጀመሪያ የለካ ጀግና ነው፡፡ ጎንደርን በደንብ ሰልሏል፡፡ ላሊበላንም በአድናቆት ለዓለም ሊነግርለት የጣረ ሰው ነው፡፡ ጥናቱ ታሪክ፥ ቋንቋና የሰው ዘር ምንጭን ቢኾንም፥ ኢትዮጵያ ከ10 ዓመታት በላይ ቆይቷል፡፡ አብዛኛውን የጥናቱን ጊዜ፥ በአድዋ ዙሪያና በተከዜ ተፋሰስ አካባቢ አሳልፏል፡፡

ይልቅዬ ከዲአባዲ ቀደም ብለው በ1832 ገደማ በፈረንሣይ መንግሥት የተላኩቱ የሳይንስ ጥናት ቡድን አባላት ፌሬትና ጋሊኒየር የአድዋ - ተከዜን፥ የተከዜ - ሊማሊሞ - ጎንደርን የጂኦሎጂ፥ የጆኦግራፊና የክላይማቶሎጂ ጥናት እንደነሱ ፈጽሞ ያጠና የለም፡፡ እንዲያውም፥ኋላ የመጣውና ከ1832 እስከ 1837 ኢትዮጵያ የቆየው የፈረንሣዩ የባሕር ኃይል መኮንን ሌፌብሬ ስለስሜን ተራሮችና ከሥሩ ስለሚፈልቀው የተከዜ ወንዝና የተፋሰስ ዙሪያ፥ 6 ሳጥን ሙሉ ታሪካዊ፥ አርኪዎሎጂአዊና ሥነ ባሕላዊ ጥንቅሮችን ማሰባሰቡ ይነገራል፡፡

እና "ተከዜ! ጉድኽ ብዙ ነው!!!" አልኩ፡፡ ይኽን ይኽን እያሰላሰልኩ - ከጥቂት ደቂቆች በኋላ - ምናልባትም ግማሽ ሰዓት ተጉዘናል - ከተከዜ ሸለቆ አቀበት አፋፍ ላይ ወጣን፡፡ "ለዛሬው ተከዜ ደኅና ኹን! ላይኽ ምፈልገው እንደ አኹኑ ውጥናችን ለምተኽ ነው!!" አልኩ፡፡

ተከዜን ከተሰናበትን ከሩብ ሰዓት በኋላ፥ ለጥ ባለ ሜዳ ላይ እየጋለብን አዲ ገብሩ ገባን፡፡ ሜዳው ይገርማል!!! አጠገቡ ተከዜን ያኽል ሸለቆና በረሀ ፈጽሞ ደብቆ፥ ደጋማና ሜዳማ መኾኑ ያስደንቃል፡፡ ከሩብ ሰዓት በኋላም ከአዲ ገብሩ አምባ ጉና ወይም ከአባ ጉና ጋራ ደረስን፡፡ ከተማዋ ደምበ ጉና መባሏን አወቅኹ፡፡ የደርግና የወያኔ ዋናውና ወሳኙ የስሜን ውጊያ ማለትም የሽሬ እንዳ ሥላሴው ውጊያ የተጠናቀቀበት መኾኑን ተረዳኹኝ፡፡

ከግማሽ ሰዓት በኋላም፥ ከለምለሙ የሽሬ አውራጃ ገባን። " ከጎጃም ወዲኽ እጅግ ለምለማማ አምባ ሽሬ ነው ማለት ነው!" አልኩኝ። እና ከሽሬ አውራጃ ዋና ከተማ እንዳ ሥላሴ ገባን። እየመሻሸ ስለነበር ገሰገስን። ወዲያውኑ ለጥቀን ሰለክለካ ገባን። ከሰለክለካ ደግሞ ውቅሮ(?) ገባን። ያ ውሃ - ውሃ - የሚያሰኝ ጉዞ ፥ ከድካም ጋር - ቀኑ ለዓይን ያዝ እያደረገ ነበር። ለካ ከዝነኛዪቱ አክሱም - ከጥንቲቱ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ አምባ - ከጽላተ ሙሴ መንበረ ምድር- ከቅድስቲቱ የጽዮን ማርያም መካን እየተቃረብን ኖሯል??! ከምሽቱ 12 ሰዓት ተኩል ላይ ከናፈቅኋት አክሱም ገባን።

*[ጊዜ ካገኘኹ የአክሱም ቆይታዬንና - የመቐለ- ደሴን ቅኝቴን ላወጋችኹ አልሰለችም። እስከዚያው በቸር ያቆየን።]*

XXXXXXXXXXXXXXXXXXXXXXXXXX